# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 185 መጋቢት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ሱልጣን አህመድ አሊሚራህ 15ኛውን የአፋር ሱልጣንነት ተቀበሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አልጋ ወራሽ ሱልጣን አህመድ አሊሚራህ 15ኛው የህውሳ ሱልጣኔት ሱልጣን የሆኑበት የበዓለ ሲመት ሥነ ሥርዓት በአፋር ክልል አሳጊታ ከተማ ተካሄደ።

የቀድሞ የአፋር ሱልጣኔት መሪ ሱልጣን ሃንፍሬ አሊሚራህ ከዓመታት በፊት ሕይወታቸው ማለፉን ተከትሎ ወንድማቸው ሱልጣን አህመድ አሊሚራህ የሱልጣንነት ሹመታቸውን ተቀብለዋል። በዕለቱም ሱልጣን አህመድ አሊሚራህ በአፋር ሱልጣኔት 15ኛው ሱልጣን መሆናቸው ተገልጿል፡፡

በሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ እንደገለጹት፤ የአፋር ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ የአንድነትና የጽናት ተምሳሌት ነው፡፡ በመሆኑም መሰል ባህላዊ ሥርዓቶችን ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፍ አኳያ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ከአፋር ሕዝብ ሊማሩ ይገባል ብለዋል፡፡

የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አወል አርባ

**ሱልጣን አህመድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# የሠራተኞችን መብት ለማስከበርና ሕገ ወጥ ስደትን ለመከላከል የአገራት ቅንጅታዊ አሠራርን ይፈልጋል

## - 4ኛው የ11 አገራት የሚኒስትሮች ፎረም መካሄድ ጀምሯል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የሠራተኞችን መብት ለማስከበርና ሕገ ወጥ ስደትን ለመከላከል የአገራት ቅንጅታዊ አሠራር እንደሚያስፈልግ ተገለጸ፡፡ በምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ የሚታየውን የሠራተኞች ፍልሰት ለመቆጣጠር የሚያስችል 4ኛው የ11 አገራት ሚኒስትሮች ፎረም በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል፡፡

በምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ የሚታየውን የሠራተኞች መብት ለማስከበርና ሕገ ወጥ ስደትን ለመቆጣጠር

**የሠራተኞችን መብት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



ፎቶ - አዩብ ተፈሪ


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

pepsi


የኢትዮጵያ የዓይን ባንክ
EYE BANK OF ETHIOPIA

# የዓይን ብሌን ለመለገስ ቃል የሚገቡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ነው

- 223 ዜጎች የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ተደርጎላቸዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የዓይን ብሌን ለመለገስ ቃል የሚገቡ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እያሳየ መምጣቱን የዓይን ባንክ አስታወቀ፡፡ በፈረንጆቹ ባለፈው አንድ ዓመት

**የዓይን ብሌን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# በአማራና አፋር ክልሎች ከ90 በመቶ በላይ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ጥገና ተደርጓል

ገጽ 4







# በደቡብ ክልል ከበጋ መስኖ ስንዴ ከ500 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

## - ከ13 ሺህ ሄክታር በላይ በዘር ተሸፍኗል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ በዘር ከተሸፈነው የበጋ መስኖ ስንዴ ከ500 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት እንደሚጠበቅ የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከ13 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ መሸፈኑ ተገልጿል፡፡

በክልሉ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ 13 ሺህ 400 ሄክታር መሬት በመስኖ ስንዴ ተሸፍኗል፡፡

በአጠቃላይ ከ36 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች በመስኖ ልማቱ እየተሳተፉ ሲሆን ከ500 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ በበጋ የመስኖ ስንዴ ልማት ከሚሳተፉ 36ሺህ አርሶ አደሮች መካከል ከ12 ሺህ በላይ የሚሆኑት ሴት አርሶ አደሮች ናቸው። 79 ባለሀብቶችም በክልሉ መሬት ወስደው የበጋ ስንዴ እያለሙ መሆናቸውን



አቶ ኡስማን ገልጸዋል፡፡

በክልሉ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ ወጣቶች በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ገጠራማ አካባቢዎች በመሄድ የመስኖ ውሃ አማራጭ ባለባቸው መሬቶች ላይ የእርሻ ሥራ እያከናወኑ ይገኛል። 4ሺህ 900 ወጣቶችም በበጋ መስኖ ስንዴ ላይ ተሰማርተዋል ሲሉም ገልጸዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ምርት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ጥረት ይደረጋል። በ2014 ምርት ዘመን በአምስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የበጋ ስንዴ ማልማት ተችሏል። ዘንድሮ ደግሞ ቁጥሩን ከእጥፍ በላይ በማሳደግ 13 ሺህ ሄክታር በላይ ማድረስ ተችሏል ብለዋል፡፡

የበጋ መስኖ ስንዴ በተሻለ ሁኔታ በለማባቸው አካባቢዎች ላይ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮች ተዘዋውረው እንዲመለከቱ በማድረግ የልምድ ልውውጥ ሥራዎች ሲከናወኑ ነበር ያሉት አቶ ኡስማን፤ ይህም የአርሶ አደሩን ግንዛቤ በማሳደግ በቀጣይ የተሻለ ምርት ለማልማት ይረዳል ብለዋል፡፡

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ምርታማነትን ከማሳደግና ድህነትን ከመቅረፍ አንጻር ሚናው ጉልህ ነው። በመሆኑም የህልውናችን ጉዳይ የሆነው የስንዴ ምርትን በማምረት ከውጭ የሚገባውን ምርት በአገር ውስጥ ለመተካት ይሠራል ሲሉ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

በክልሉ ያሉትን የውሃ አማራጮች አርሶ አደሩ በተቻለው መጠን እንዲጠቀምባቸው እና ስንዴ በበጋ መስኖ እንዲለማ በማድረግ በኅብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ መነቃቃት መፈጠሩንም አስረድተዋል፡፡

# በኦሮሚያ ክልል በመጪው የክረምት ወቅት አምስት ቢሊዮን የሚጠጉ ችግኞች ይተከላሉ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በመጪው የክረምት ወቅት አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በመጪው የክረምት ወቅት አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ እስከ አሁን ድረስ ሦስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል።

ባለፈው የክረምት ወቅት አራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸውን ያስታወሱት ኃላፊው፤ በዘንድሮ ክረምት ለመትከል ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር የ400 ሚሊዮን ችግኞች ብልጫ እንዳለው ጠቁመዋል። ባለፈው ዓመት የተተከሉት ችግኞች የጽድቀት መጠናቸው ሲገመገም ከቦታ ቦታ እንደሚለያይ የተናገሩት አቶ ጌቱ፤ የተተከሉት ችግኞች በአብዛኛው መጽደቃቸውንና እንደ ክልል የመጀመሪያው ግምገማ የሚያሳየው 92 በመቶ መጽደቃቸውን ተናግረዋል።



አቶ ጌቱ ገመቹ

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በዘንድሮው ክረምት የሚተከሉት ችግኞች በአብዛኛው ፍሬያቸው እና ቅጠላቸው ለምግብነት ሊውሉ የሚችሉ ናቸው። ከዚህ በፊት በችግኝ ተከላ ወቅት ያልተተከሉ እንደ ጊሽጣ እና ቴምር የመሳሰሉ ችግኞች ለመጀመሪያ ጊዜ ለመትከል ተዘጋጅተዋል። ሽምበቆም ለተለያዩ የእንጨት ሥራዎች የሚውል በመሆኑ ከተዘጋጁ ችግኞች መካከል ነው። አቮካዶ እና ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ ዕጽዋቶችም ይተከላሉ።

የችግኝ ተከላ ሥራው የሚጀመርበት ወቅት ከቦታ ቦታ የሚለያይ ሲሆን የበልግ እና የክረምት ዝናብ የሚያገኙ አካባቢዎች ከሚያዝያ ጀምሮ ወደ ሥራ ይገባል። ሌሎቹ አካባቢዎች ደግሞ ከሰኔ ጀምሮ እስከ ነሐሴ 15/2015 ዓ.ም ወደ ሥራ እንደሚገቡ ኃላፊው ተናግረዋል።

ከችግኝ ዝግጅቱ በተጨማሪም በክልሉ ሌሎች የተፋሰስ ልማት ሥራዎችም በጥሩ ሁኔታ እየተካሄዱ ነው። ሥራው በ21ዱም ዞኖች በስፋት እየተሠራ እንደሆነና አጠቃላይ ትኩረቱ የአፈር እና የውሃ ጥበቃ ሥራ ላይ ሆኗል። ለዚህም ስኬት የ60 ቀናት ሥራ በማስጀመር ወደ ሥራ ተገብቷል።

ለ60 ቀናት ታቅዶ እየተሠራ ባለው ሥራ እስከ አሁን የሥራው 85 በመቶ መጠናቀቁንና 837 ሺህ ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የተፋሰስ ልማት ሥራ መሠራቱን የሚናገሩት አቶ ጌቱ አሁንም በስፋት እየተሠራበት እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

# በከተማዋ የተከሰተው የኃይል መቆራረጥ ምክንያት በነባር መስመሮች ላይ የደረሰ ብልሽት ነው

## - አገልግሎቱ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እየሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ የተከሰተው የኃይል መቆራረጥ በነባር መስመሮች ላይ በደረሰ ብልሽት ምክንያት መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ ክፍሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሰሞኑን በአዲስ አበባ አንዳንድ አካባቢዎች ተፈጥሮ የነበረው የኃይል መቆራረጥ ችግር በዘነበው ከፍተኛ ዝናብ ምክንያት በነባር መስመሮች ላይ በደረሰ ብልሽት ነው። ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት አገልግሎቱ በትኩረት እየሠራ ነው።

በንፋስ እና በዝናብ ምክንያት በተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥ እንደሚያጋጥም የገለጹት አቶ በቀለ፤ የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች ለረዥም ዓመታት ያገለገሉ በመሆናቸው ከባድ ዝናብ ሲጥል ጉዳት ስለሚደርስባቸው መቆራረጥ እንደሚፈጠር አብራርተዋል፡፡ በተለይም ለዚህ ችግር በኤሌክትሪክ ማሠራጫ ገመዶች አካባቢ የሚገኙ ዛፎች መንስዔ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ የኤሌክትሪክ መስመሮችን የሚነካ ዛፍ በሚኖርበት ወቅት በአካባቢው ለሚገኝ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል በማሳወቅ መተባበር ይገባል ያሉት የኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስኪያጁ፤ በአሁኑ ወቅት አብዛኞዎቹ መጋቢ መስመሮች ተጠግነው አገልግሎቱ ወደ ነበረበት ተመልሷል ሲሉ ገልጸዋል። ቀሪዎቹን አካባቢዎች ደግሞ በፍጥነት ለማገናኘት በዲስትሪክቶች በኩል የኤሌክትሪክ ኃይል የተቋረጠባቸውን መስመሮች የመጠገን ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በምሰሶዎች ላይ የሚያጋጥም የመኪና ግጭት፣



አቶ በቀለ ክፍሌ

የዛፍ መውደቅ፣ በግንባታና መንገድ ሥራዎች ወቅት ከሚከሰት የኤሌክትሪክ ሽቦ መቆረጥ ጋር በተገናኘ መብራት እንዲቋረጥ ምክንያት እንደሚሆኑ ገልጸው፤ በክረምት የሚከሰቱ መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ የቅድመ ጥገና ሥራዎች በሰፊው እየተሠሩ መሆኑን ገልፀዋል።

ካለፉት ጥቂት ቀናት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ በመከሰቱ ኅብረተሰቡ ቅሬታ ሲያሰማ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

# የሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እየተሻሻለ መጥቷል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ምክትል ፕሬዚዳንትና የፌዴራል የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ማቋቋም አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ጠይባ ሐሰን ገለጹ።

ወይዘሮ ጠይባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በታሪክ የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ ወደ 50 በመቶ የተጠጋበትና እንደ አሁኑ ሴት የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር የሆነችበት ጊዜ ታይቶ አይታወቅም። ሀብት ከማፍራትና በመምራት ረገድም ሴት ባለሀብቶችን ለማፍራት እየተደረገ ባለው እንቅስቃሴ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል።



ወይዘሮ ጠይባ ሐሰን

ቀደም ሲል ከባድ ኃላፊነት ነው በማለት ለወንዶች ብቻ የሚሰጡ እንደ ፕሬዚዳንትነትና ሚኒስትርነት ያሉ አገራዊ ኃላፊነቶች በስፋት ለሴቶች መሰጠታቸውን ያወሱት ወይዘሮ ጠይባ፤ ሴቶቹም በተሰጣቸው ኃላፊነት አበረታች ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውንና ባሉበት የሥራ ኃላፊነት ሚናቸውን በሚገባ እየተወጡ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ሴቶች ተሳትፏቸውን በማሳደግ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቷ፤ ከዚህ አንጻር በተለይ ሴቶችን ከኢኮኖሚ ጥገኝነት በማላቀቅ በተለያዩ የሥራ መስኮች ለማሳተፍ እየተደረገ ያለው ጥረት የሚያበረታታ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ያለብቃት ሴቶችን በሴትነታቸው ብቻ በኮታ ማሳተፍ እንደሌለበት የመከሩት ወይዘሮ ጠይባ፤ ሴቶች ራሳቸውን ችለው በሁሉም የሥራ ኃላፊነት መስኮች ተሳታፊነታቸውን ማሳደግ እና በተለይ ለሴቶች እየተሰጠ ያለውን የትምህርት ዕድል ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ጠይባ ማብራሪያ፣ የአገር ወይም የሥራ መሪ መሆን ማለት የውጤትና የተግባር እንጂ የሥራ መለማመጃ መሆን የለበትም። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ መንግሥት በትምህርት ላይ በስፋት ኢንቨስት በማድረጉ በርካታ የተማሩና ብቃት ያላቸው ሴቶች ማፍራት ተችሏል። እንደከዚህ በፊቱ የተማሩ ወስን ሴቶች በባትሪ የመፈለግ አሊያም ብቁ ያልሆኑትን የማለማመድ ምዕራፍ አይታይም፤ መኖርም የለበትም። የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግም የሴቶችን አቅም ለማጎልበት የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ሥራዎችን እየሠራ ነው።

እንደ ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ማቋቋም አገልግሎትም ከስደት ጋር ተያይዞ ለሚፈጠሩ ችግሮች አብዛኛው ተጋላጭ ሴቶች በመሆናቸው በአገራቸው ሠርተው እንዲለወጡ የተለያዩ ድጋፎች መደረጋቸውን የተናገሩት ወይዘሮ ጠይባ፤ ስደተኞቹን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ማቀላቀል አንዱ የማቋቋም አካል በመሆኑ በርካታ ሴቶች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የማቀላቀል ሥራ መሠራቱን አመልክተዋል።

ከሳውዲ ዓረቢያ ብቻ የተመለሱ ዜጎች ወደ አንድ ሚሊዮን ገደማ መሆናቸውን ያብራሩት ወይዘሮ ጠይባ፤ ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ ዜጋ በአንድ ጊዜ የሥራ ዕድል መፍጠር ባይቻልም የተወሰኑትን በተለይ ሴቶቹን ለመደገፍ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ፈንድ የማፈላለግ እና ሥልጠና የመስጠት እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።



ዶክተር ታረቀኝ ብርሃኑ

# ዩኒቨርሲቲው በቴክኖሎጂና በሳይንስ ዘርፍ ተግባር ተኮር የምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ካለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ በቴክኖሎጂና በሳይንስ ዘርፍ ተግባር ተኮር የምርምር ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ታረቀኝ ብርሃኑ እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ለማግኘት ባለፉት ሦስት ዓመታት በርካታ የፈጠራ ሥራዎችን እያከናወነ ቆይቷል። በሚቀጥለው ዓመት በአሜሪካ አገር በሚገኙ «ዋሽንግተን አኮርድ» እና «አቤት» ለሚባሉ እውቅና ሰጪ ተቋማት ለማመልከት ዝግጅት እያደረገ ነው።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ፤ ዩኒቨርሲቲው ዕውቅናውን ካገኘ የሚያስተምራቸው ተማሪዎች ዓለም አቀፍ መሐንዲሶች፣ ተመራማሪዎችና ሳይንቲስቶች ይሆናሉ። በየትኛውም አገር በመሄድም መቀጠር ይችላሉ። መንግሥትም የትምህርት ሥርዓቱን በዚህ መልኩ እየቀረጸ ነው። ኩረጃን ማጥፋትና የትምህርት ጥራትን ለማሳደግ የሚደረግ ዘመቻ ሁሉ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠትና ተማሪዎች ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲኖራቸው ለማስቻል በማሰብ ነው ብለዋል።

በኢንጅነሪንግ የትምህርት ዘርፎች ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች ኢንጂነሪንግ ቲም ፕሮጀክት የሚል ኮርስ መጀመሩን ያነሱት ዶክተር ታረቀኝ፤ ይህም የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ለአገራቸውና ለራሳቸው የሚጠቅም እና ገንዘብ የሚያስገኝ ነው።

የተለያዩ ሙያተኞች ተቀናጅተው መሥራት አለመቻላቸው እንደ አገር የሚጎድለን ነገር ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በየሙያቸው በየራሳቸው መንገድ ከመሮጥ ወጥተው ችግር ፈቺ ሥራዎች እንዲሠሩ የተቀናጀ የቡድን ተኮር ሥልጠና መጀመሩን አብራርተዋል። ዘርፉ ወደ ፊትም በልዩ ትኩረት የሚሠራበት የትምህርት ክፍል ሆኖ ይቀጥላል ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው ተቋም መመስረት ከተቻለ ለአገር ከፍተኛ አበርክቶ ያላቸውን ተማሪዎች መፍጠር ይቻላል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ይህን ለማድረግ ከኢንዱስትሪ ተቋማት ጋር አብሮ መሥራት እንደሚጠይቅ ጠቁመዋል።

ዩኒቨርሲቲው ትኩረቱ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በመሆኑ ለተማሪዎች የሚሰጠውን ትምህርት ተግባር ተኮር ማድረግ ስላለበት የላቦራቶሪና የወርክሾፕ ዝግጅት በብዙ እንደሚፈለግ ጠቅሰው፤ ይህንን ለማሳካት በዕቅድና በስፋት እየሄድንበት ነው ብለዋል። ተማሪዎች በርካታ የፈጠራ ሥራዎችን በመሥራት እንደ አገር ያሉብንን የቴክኖሎጂ ችግሮች ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ሲቋቋም ኢንዱስትሪውን እንዲያግዝ ተብሎ ነው ያሉት ዶክተር ታረቀኝ፤ ኢንዱስትሪዎች ያሉባቸውን ችግሮች በተግባር በመለየት የመፍትሔ አማራጮችን ለማቅረብ አሠራሮችን ዘርግቷል ብለዋል።



# ከተማዋን የኢንቨስትመንትና የኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው

**በመሠረት በኃይሉ**

ደብረ ታቦር፡- የደብረ ታቦር ከተማን የኢንቨስትመንት እና የኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን የከተማዋ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ መምሪያ ገለጸ።

የደብረ ታቦር ከተማ የኢንቨስትመንት እና የኢንዱስትሪ መምሪያ ኃላፊ አቶ አባይነው አሸብር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተማዋ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የኢንዱስትሪ ባለቤትነቷን አጥታ ቆይታለች። ይሁንና መምሪያው አሁን ላይ ከተማዋን የሚመጥኑ የልማት ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

በንጉሡ እና በደርግ ዘመን የነበረውን የአውሮፕላን ማረፊያ እንደገና በማስፋፋት በአዲስ መልክ ሥራ ለማስጀመር ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህም ኢንቨስትመንትን ወደ ከተማዋ ለመሳብ የራሱ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አባይነው ገለጻ፤ የአካባቢውን የተፈጥሮ ጸጋ በመጠቀም የቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እየተሠራ ነው። በተለይ በእንጨት፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ ስጋና ወተት፣ ሲሚንቶ እና የቢራ ብቅል፣ ማዕድንና መሰል ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶችን ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

ከተማዋ በተለያዩ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች እና ጥያቄ ለሚያቀርቡ ሁሉ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆኗን የተናገሩት ኃላፊው፤ የአገልግሎት አሰጣጡ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሻሻለ መሆኑን ጠቁመዋል።

በከተማዋ ለሆቴልና ሪዞርት እንዲሁም በማኑፋክቸሪንግ እና ሎጅ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቂና ሰፋፊ ቦታዎች መዘጋጀታቸውንም አክለው ተናግረዋል።

እንደ አቶ አባይነው ገለጻ፤ የከተማዋን እምቅ ሀብት ለማስተዋወቅ እስካሁን በኤሌክትሮኒክስ እና በህትመት ሚዲያዎች ጥረት በመደረግ ላይ ነው። ይህን ተከትሎ ጥቂት ባለሀብቶች ከተማዋ ላይ ኢንቨስት ያደረጉ ሲሆን ሌሎች ባለሀብቶችም ጥያቄ እያቀረቡ ይገኛሉ።

የአካባቢውን ደህንነት በዘላቂነት ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀራረብ እየተሠራ መሆኑን ነው የተናገሩት። የደብረ ታቦር ከተማ ሜትሮ ፖሊታን ሲቲ በመሆን ቀጥታ ተጠሪነቱ ለአማራ ክልል መንግሥት መደረጉ የሚታወስ ነው።



አቶ ካሳሁን ፎሎ

# ስደተኞች ኑሯቸው እንዲሻሻል እና መብታቸው እንዲከበር እየተሠራ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከአገራቸው ውጪ የሚኖሩ ስደተኞች ኑሯቸው እንዲሻሻል እና መብታቸው እንዲከበር ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የአፍሪካ ቀንድ የሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን አስታወቀ።

የአፍሪካ ቀንድ የሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ካሳሁን ፎሎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከአገራቸው ውጪ የሚኖሩ ስደተኞችን ኑሮ የተሻለ እንዲሆንና መብቶቻቸው እንዲጠበቁላቸው ለማድረግ የአፍሪካ ቀንድ የሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን በመካከለኛው ምሥራቅ አገራት ከሚገኙ የሠራተኞች ማህበራት ጋር ስምምነቶችን እየተፈራረመ ነው።

ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚሰደዱ ስደተኞች በብዛት ከኢጋድ አባል አገራት የሚሄዱ በመሆናቸው በተቀባይ አገራት የሠራተኞች መብት ተጠብቆላቸው እንዲሠሩ ለማድረግ የጋራ መመሪያ አውጥተው እየሠሩ ነው።

በስደተኞች ተቀባይና በላኪ አገራት መካከል ስምምነት ስለሚደረግበት ሁኔታ በጂቡቲ ስምምነት ውስጥ ተካቷል ያሉት አቶ ካሳሁን፤ ስምምነቱ እያንዳንዱ አገራት ከመካከለኛው ምሥራቅ አገራት ጋር በተናጠል ስምምነት ይፈጽማል። ነገር ግን የጂቡቲው ስምምነት እንደ መመሪያ በመሆን የጋራ የሆነ አሠራር እንዲኖር የሚጠቅም ነው። ይህም መመሪያ ለኢጋድ አባል አገራት በሙሉ ይሠራል። የሠራተኞችን መብትም ለማስከበር ዓይነተኛ ሚና እንደሚኖረው አብራርተዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ፤ ከመንግሥት ውጭ ከተቀባይ አገራት ካለው የሠራተኞች ማኅበር ጋር በመፈራረም የሠራተኞች መብት እንዲጠበቅ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች አሉ። የአፍሪካ ቀንድ የሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን ከአረብ አገራት ሠራተኛ ኮንፌዴሬሽን ማህበር ጋር እየተፈራረመ ነው። እንዲሁም የየአገራቱ የሠራተኞች ማህበር ከእያንዳንዱ አገር ጋር እንዲፈራረሙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው። ይህንንም ኢትዮጵያና ኬንያ መጀመራቸውን ገልጸዋል።

በውጭ አገር ያሉ ሠራተኞች መብቶቻቸው እንዲከበሩላቸው ሠራተኞችን በማደራጀት ካሉበት አገር የሠራተኛ ማህበር ጋር የማገናኘት ሥራ መሠራት እንደተጀመረ የገለፁት አቶ ካሳሁን፤ ይህም ሠራተኞች ለሚሠሩት ሥራ ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፈላቸው እንዲሁም መብቶቻቸውን እንዲከበሩላቸው እንደሚያደርግ ገልጸዋል። ይሁን እንጂ በአንዳንድ አገራት የሠራተኛ ማህበር ባለመኖሩ አስቸጋሪ ሁኔታ መኖሩንም አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ከኩዌት ጋር ስምምነትን በመፈራረም የዜጎቿን መብት ለማስጠበቅ እየሠራች መሆኑን የገለጹት አቶ ካሳሁን፤ በቀጣይም ከሌሎች የአረብ አገራትም ጋር ተመሳሳይ ስምምነት ትፈራረማለች ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፤ የኑሮ ሁኔታውን ያገናዘበ ክፍያ ማግኘት ከተቻለ አገሩን ጥሎ መሰደድን የሚፈልግ ዜጋ የለም። የመደራጀትና የሠራተኛው ክብር የተከበረበት የሥራ ዕድል በመፍጠር ስደትን መቆጣጠር ይቻላል። በአገር ውስጥ አስፈላጊው ሁሉ ተሟልቶላቸው ለተሻለ የሥራ ፍለጋ ከአገራቸው ለሚወጡት ደግሞ ከመሄዳቸው በፊት ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል።

በኢጋድ አባል አገራት የተፈረመው ስምምነት የሥራ ዕድል ፈጠራን ያጠቃልላል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በምሥራቅ አፍሪካና በአፍሪካ ቀንድ ያለው የሥራ አጥነት ቁጥር ከፍተኛ ነው። በግጭትና በጦርነት የሚታመስ ቀጣና በመሆኑ ድህነት ስር የሰደደበት ነው። ግጭት ሲኖር ስደት አለ፤ ስደትን ለመግታት በቀጣናው መረጋጋትንና ሰላም መፍጠር አስፈላጊ እንደሆነ አንስተዋል።

# በአማራና አፋር ክልሎች ከ90 በመቶ በላይ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ጥገና ተደርጓል

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ተከስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሥራ ለማስጀመር አስፈላጊው በጀትና የሰው ኃይል በመመደብ ከ90 በመቶ በላይ ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት እንደጀመረ ተገለፀ፡፡

የአማራ ክልል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰለሞን ጣሰው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ጉዳት የደረሰባቸው አብዛኞቹ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታዎች መሬት ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ለከፍተኛ ውድመትና ስርቆት መዳረጋቸውን በማስታወስ፤ የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ሰፊ ሥራ መሠራቱን ገልፀዋል፡፡

የተከሰተው የኤሌክትሪክ አገልግሎት መቋረጥ ለተቋሙና ለአገር ትልቅ ኪሳራ ያስከተለ ከመሆኑም ባሻገር ለሌላ ኢንዱስትሪና ልማት ዝርጋታ የሚውል ከፍተኛ በጀት መልሶ ለመጠገን ሥራ መዋሉን አስረድተዋል፡፡



ኢንጂነር ያሲን ዓሊ



አቶ ሰለሞን ጣሰው

የአፋር ክልል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሥራ አስፈፃሚ ኢንጂነር ያሲን ዓሊ በበኩላቸው፤ በከተሞች እንዲሁም በወረዳዎች ላይ የነበሩ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ ንብረቶች ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው ገልጸው፤ እነዚህን መልሶ ለመጠገን በርካታ ካፒታል እና የሰው ኃይል ወጥቷል ነው ያሉት፡፡

እንደ ሥራ አስፈፃሚው ገለፃ፤ ከሰላም ስምምነት በኋላ በየሳይቶቹ በመግባት የወደሙ ንብረቶችን ከማወቅ ጎንለጎን የጥናት ሥራዎች ሲሠሩ በመቆየታቸው የኤሌክትሪክ ዝርጋታው በፍጥነት እንዲሠራ አግዟል ብለዋል፡፡

በአፋር ክልል ዞን ሁለት ላይ በሦስት የአገልግሎት መስጫዎች ማለትም አብዓላ፣ በራሕሌ እና ኮነባ ሙሉ በሙሉ ከነሳተላይታቸው እንዲገናኙና በፊት ከነበረው የእንጨት ምሰሶ ወደ ኮንክሪት በመቀየር የበለጠ የማሻሻል ሥራ ተከናውኗል ያሉት ኢንጂነር ያሲን፤ በአንፃሩ ዳሎል እና ረብቲ የተባሉ ሁለት ወረዳዎች አገልግሎቱን እስከ አሁን እንዳላገኙ በመግለፅ አገልግሎቱ በቀጣይ ከአፍዴራ ሰብስቴሽን እንደሚዘረጋ ጠቁመዋል፡፡

# የሠራተኞችን መብት ለማስከበርና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የቀጣናው አገራት የሚኒስትሮች ፎረም በአዲስ አበባ ትናንት መካሄድ ጀምሯል።

በፎረሙ መክፈቻ ላይ የዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት በኢትዮጵያ ምክትል ኃላፊ ዣን ዡ፤ ስደት ለመቆጣጠርና የስደተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ ፖሊሲዎችንና ልምዶችን መቀመር አስፈላጊ ነው። የሠራተኛ ፍልሰት በምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ ላሉ አገራት ፈታኝ በመሆኑ ፎረሙ ለዚሁ ሥራ ጠቀሜታ አለው።

ፎረሙ በቀጣናው ውስጥ ላሉ መንግሥታት ሀሳቦችንና አሠራሮችን ለመለዋወጥ፤ የሠራተኛ ፍልሰትን ለመቆጣጠር፤ የስደተኞችንና ሠራተኞች ደህንነት ለመጠበቅ፤ ፖሊሲዎችንና ልምዶችን አስተሳስሮ ለመምራት የሚያስችል ወሳኝ መድረክ ነው። የዚህ ዓመት የፎረሙ መሪ ሀሳብ «የሠራተኛ እንቅስቃሴ፣ የስደት አስተዳደርና የቀጣናው ውህደት» በሚል የሚካሄድ ነው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ የሁለትዮሽ የሠራተኛ ፍልሰት ዝግጅቶች፣ የስነምግባር ቅጥር የዓለም አቀፍ የስደት ህግና የስደተኛ ሠራተኞች መብቶች፣ ክህሎት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፤ የሥርዓተ-ፆታ፣ የዳያስፖራና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ፤ የሠራተኞች ትብብር ለስደተኛ ሠራተኞች ጥበቃ ዙሪያ ጠቃሚ ውይይት እንደሚደረግባቸው ገልጸዋል።

ዣን ዡ እንደለገጹት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለፉት ዓመታት የስደት አስተዳደርን ለማሻሻል ያደረገውን ጥረት በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተመዘገቡት ውጤቶች የሚደነቁ መሆናቸው ተናግረዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አሰግድ ጌታቸው በበኩላቸው፤ አራተኛው የሚኒስትሮች ፎረም በሠራተኞች መብት አያያዝ፣ ጉልበት ብዝበዛን በመከላከል፣ ሕገወጥ ፍልሰትን ለመቆጣጠር አገራት ያላቸው ልምዶችና ተሞክሮዎችን የሚለዋወጡበት ነው። መድረኩ ኢትዮጵያ በሠራተኞች አያያዝና በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ያላትን ልምድና ተሞክሮ እንደምታካፍል ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሠራተኞች ፍልሰት ፎረም ሊቀመንበርነትን ባለፈው ዓመት ከኬያን ተቀብላ እየመራች መሆኑን የገለጹት አቶ አሰግድ፤ በቀጣናው የተከበረና ሰብአዊነትን የተላበሰ የፍልሰት አስተዳደርን የማረጋገጥ ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው። የሠራተኛ ፍልሰት ችግሮችን በጋራ ለመፍታት፣ የሠራተኛ እንቅስቃሴን ለማጎልበት፤ የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ላይ የሚስተዋለውን የሠራተኞች ሕገ ወጥ ፍልሰትን ለመቆጣጠር አገራት በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል።

አቶ አሰግድ፤ ከሥራ ጋር ተያይዞ ዜጎች ወደ ተለያዩ አገራት ሲሄዱ ፲፩ዱ አባል አገራት በጋራ ሆነው የዜጎቻቸውን ጥቅም ማስከበር የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይት ይደረጋል። ዜጎች ለሥራ ሲሄዱ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ውይይት ነው። በተለይም ከደመወዝ፣ ከዓመት እረፍት፣ ከሥራ ላይ ደህንነት፣ የተለየ ጫና የበዛበት ሥራ እንዳይሠሩ በጋራ ለመከላከልና የዜጎችን ጥቅም በጋራ ለማስጠበቅ ያስችላል። ይህንን ለማድረግ ፖሊሲና ስትራቴጂ መዘጋጀቱንም ጠቁመዋል።

ፎረሙ ፲፩ አገራትን ማለትም ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ቡሩንዲ፣ ኤርትራ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ሩዋንዳ፣ ሶማሊያ፣ ታንዛኒያና ኡጋንዳን ያካተተ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ ተወካዮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በፎረሙ ተገኝተዋል።

# ሱልጣን አህመድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በበኩላቸው፤ የአፋር ሕዝብ የበርካታ ታሪካዊ ባህሎች ባለቤት መሆኑን አንስተው፤ ከእነዚህም ውስጥ የሱልጣኔት ሥርዓት አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ሥርዓት በተለይ የማኅበረሰቡን መብት ከማስጠበቅ አኳያ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የሱልጣን አሕመድ አሊሚራህ አባት ሱልጣን አሊሚራህ የተለያዩ ጎሳዎች የእኩል ተጠቃሚነት መብታቸው እንዲከበርና በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ፍትሃዊነት እንዲረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከታቸውን በመግለጽ፤ ሱልጣን አህመድ አሊሚራህም የአባታቸውን ተግባር እንደሚደግሙ ያላቸውን እምነትም ገልጸዋል።

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ በሥነ ሥርዓቱ ላይ አፋር ክልል የሰው ዘር መገኛ መሆኑን አንስተው በዚህም የአፋር ማህበረሰብ ሥርዓቱን ተንከባክቦ ለትውልድ ማሸጋገር እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

የሱልጣንነት ሲመቱን የተቀበሉት ሱልጣን አህመድ አሊሚራህ በበኩላቸው፤ በማኅበረሰቡ የጎሰኝነት አስተሳሰብ ተቀርፎ ሁሉም በአንድነት ወደ ልማት ጎዳና እንዲሰማራ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ከሕዝቡ ጎን በመቆም እንደሚሠሩ ተናግረዋል።

በሥነ-ሥርዓቱ የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ አመራሮች፤ የተለያዩ አገራት አምባሳደሮች፣ የጎረቤት አገራት ተወካዮች፣ የሃይማኖት አባቶች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተሳትፈዋል፡፡

# የዓይን ብሌን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

223 ዜጎች የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ እንደተደረገላቸው ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ዓይን ባንክ የግንዛቤ ማስጨበጫ አስተባባሪ አቶ ነጋ ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በፈረንጆቹ ባለፈው ዓመት 191 ዜጎች ለመለገስ ቃል ገብተዋል። በተለይም ከታዋቂው አርቲስት ታሪኩ ብርሀኑ ህልፈት በኋላ 80 ሰዎች ቃል የገቡ በመሆኑ የዓይን ብሌን ለመለገስ ቃል የሚገቡ ሰዎች ቁጥር መሻሻል አሳይቷል። በዚህም በፈረንጆቹ ባለፈው አንድ ዓመት 223 ዜጎች የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ተደርጎላቸዋል።

እንደ አቶ ደምሴ ገለጻ፤ ከ16 ዓመት በፊት በተደረገ ጥናት በአገር አቀፍ ደረጃ ሁለቱም ዓይናቸው በዓይን ጠባሳ ተያያዥ ምክንያት ለዓይነ ስውርነት የተጋለጡ 300 ሺህ በላይ ሰዎች መኖራቸውን የሚገልጽ ነው።

ባንኩ የማህበረሰብ ተቋም በመሆኑ ህልፈት ካጋጠመ በኋላ የዓይን ብሌንን መለገስ ባህሉ ያደረገ ስልጡን ማህበረሰብ መገንባት ለነገ የማይባል ተግባር መሆኑን አቶ ደምሴ ገልጸዋል።

የዓይን ባንክ፤ የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል የሚገቡ ሰዎችን በማስተናገድ ላይ ነው ያሉት አስተባባሪው ለሠርግ፣ ለልደት፣ እንዲሁም በተለያዩ ዝግጅቶች በግለሰብም ይሁን በቤተሰብ አማካኝነት ዜጎች የዓይን ብሌን ለመለገስ ቃል በመግባት ላይ ናቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የበጎ አድራጎት ተቋማት፣ የጉዞ ማህበራት፣ የስፖርት ደጋፊዎች በኅብረት ቃል ገብተዋል። በሌላ በኩል ታዋቂ አርቲስቶች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ ጋዜጠኞች ቃል በመግባት ላይ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የዓይን ብሌን በአዲስ አበባ ብቻ የሚሰበሰብ በመሆኑ በክልል ከተሞች የሚገኙ ዜጎች በአካል በመምጣት የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ቃል በመግባት ላይ ናቸው። ካሉበት ቦታ ሆነው በቀላሉ ቃል መግባት የሚችሉበትን መንገድ ለማመቻቸትም ጥረት እየተደረገ መሆኑን የተናገሩት አቶ ደምሴ፤ ባንኩ ሆስፒታልን መሠረት ያደረገ የዓይን ብሌን ስብሰባ መርሃግብር መኖሩን በመግለጽ በጥቁር አንበሳ፣ ቅዱስ ጳውሎስና ራስ ደስታ ሆስፒታሎች ላይ ህልፈት ሲያጋጥም በሕይወት ያለው ሰው ፈርሞ የዓይን ብሌኑን መስጠት እንዲችል ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን አስረድተዋል።

ለዓይን ብሌን ማቆያነት የሚያገለግል መድኃኒት በዓለም አቀፍ ደረጃ እጥረት ይከሰታል። በሌላ በኩል ምርመራ የሚደረግበት ማሽን አንድ ብቻ በመሆኑ ችግሮች ከተፈጠሩ ሥራ የሚቆምበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል አቅም ያላቸው ሰዎች ለባንኩ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋም የሀገሪቱን እምቅ የመሬት፣ የውሃና የሰው ኃይል ሀብት አቀናጅቶ መሥራት ይገባል!

ኢትዮጵያ በግብርናው መስክ ምርትና ምርታማነት እያደገባት ትገኛለች። ግብርናው የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት የጀርባ አጥንት መሆኑ ቀጥሏል፤ ዘርፉ የሀገሪቱን የምግብ ፍጆታ ከመሸፈን አልፎ፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት በኩልም ተጠቃሽ መሆኑን ቀጥሏል።

ባለፈው በጀት ዓመት ቡና አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር በማስገኘት ከዘርፉ መሪ የሆነበትን ሁኔታ ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል። የሆርቲካልቸር ዘርፍም በተመሳሳይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ችሏል። በተያዘው 2015 በጀት ዓመት ባለፉት ሰባት ወራትም እነዚህ ዘርፎች በውጭ ምንዛሪ ግኝታቸው ተጠቃሽ መሆን ችለዋል።

በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እየተመዘገበ ያለው ውጤትም ሌላው የዘርፉ ለውጥ ማሳያ ነው። ባለፈው በጀት አመት 26 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በበጋ መስኖ ማግኘት ተችሏል፤ ዘንድሮ ይህን አኃዝ 52 ሚሊዮን ለማድረስ እየተሠራ ነው።

ሀገሪቱ በስንዴ ልማት ላይ ክረምት ከበጋ እያከናወነች ያለችው ውጤታማ ተግባር ሀገራዊ የስንዴ ፍጆታዋን በራሷ እንድትችል አድርጓል፤ ይህን ተከትሎም ስንዴ ከውጭ ማስገባት አቁማለች። ስንዴ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ችላለች።

በግብርናው ዘርፍ ሃገሪቱ ይህን ያህል ርቀት መጓዝ ብትችልም፣ በሀገሪቱ እየተመላለሰ ከሚከሰት የድርቅ አደጋና ከሚያስከትለው ችግር መውጣት ግን አልቻለችም። ዛሬም ድርቅ የአርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ሕይወት እየፈተነ ይገኛል። ባለፈው ዓመት በሶማሌና በኦሮሚያ ክልል የተወሰኑ ዞኖች የተከሰተው ድርቅ አርሶ እና አርብቶ አደሮችን በእጅጉ ፈትኗል፤ የእነዚህ ወገኖች ለጋሽ እጆች ለእርዳታ ፍለጋ ተዘርግተዋል፤ እንደ ዓይናቸው ብሌን የሚመለከቷቸውን ከብቶቻቸውን ዓይናቸው እያየ ድርቁ ጨርሶባቸዋል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እንስሳት ማለቃቸውን ነው መረጃዎች ያመለከቱት።

ዘንድሮም በተመሳሳይ በሶማሌ፣ ደቡብና ኦሮሚያ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች ድርቁ ተከስቷል። ድርቁ በተለይ የኦሮሚያ ክልሉን የቦረና ዞን ክፉኛ መትቶታል። በዚህም ምንም እንኳ በድርቁ የሞተ ሰው ባይኖርም የዞኑ ሕዝብ ለከፍተኛ ጉዳት መዳረጉን ተከትሎ እርዳታ ጠባቂ ለመሆን ተገዷል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እንስሳቶቹም አልቀዋል።

በሃገሪቱ ለሚከሰተው ድርቅ ምክንያቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታየው የአየር ንብረት ለውጥ መሆኑ ይታመናል። ይህን ችግር መፍታት የሚቻለው በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄድ ዘላቂነት ያለው ርብርብ ነው።

ይህ ችግር በሰዎችና በእንስሳቶቻቸው ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት በመቀነስ በኩል ግን መሥራት ይቻላል፤ በድርቅ በተደጋጋሚ የተጠቃችው ኢትዮጵያ በዚህ በኩል ተሞክሮውም አላት። በአካባቢ ጥበቃ ወይም ተፋሰስ ልማትና በመሳሰሉት ላይ መሥራት አንዱ መፍትሔ ተደርጎ ሲሠራበት ቆይቷል። አርሶ አደሮችን በዚህና በሌሎች የሴፍቲኔት መርሐ ግብሮች በማሳተፍ ተጨማሪ ገቢ ሊያገኙባቸው የሚችሉ ሥራዎችን እንዲሠሩ በማድረግ ጥሪት እንዲያፈሩ ሲሠራ ቆይቷል። ይህን ተከትሎም በአካባቢዎቹ በአርሶ አደሮች ሕይወት ላይም ለውጥ ማምጣት የተቻለባቸውም ሁኔታዎች እንዳሉ ይታወቃል።

አሁን ድርቁ እንዲከሰት ያደረገው ምክንያት ካለፉት ድርቅ መነሻዎች ይለያል፤ ድርቁ የተከሰተው ላለፉት ሦስትና ከዚያ በላይ ዓመታት በቦረና አካባቢ መጣል የነበረበት ዝናብ ሳይጥል በመቅረቱ ነው። እንዲህ በተከታታይ ጊዜ ዝናብ በሚጠፋበት ሁኔታ የሚከሰተው ድርቅ የከፋ ችግር ሊያደርስ እንደሚችል አሁን በቦረና ዞን ከደረሰው ድርቅና ካስከተለው ጉዳት መገንዘብ ይቻላል።

ድርቅ የሚያስከትለውን ችግር የሚቋቋም ጥሪት ቢቋጠር እንኳ እንዲህ አይነቱ ድርቅ የሚያስከትለውን ችግር መመከት ይከብዳል። ሌላ ሰፊ ሥራ ማከናወን እንደሚያስፈልግ ችግሩ ያመለክታል።

ቀጣዩ መፍትሔውም ከእስከ አሁኖቹ መፍትሔዎች የሰፋ መሆን ይኖርበታል። እንደሚታወቀው፤ ሀገሪቱ ለእርሻ ሊውል የሚችል በቂ መሬት፡ የሰው ሀብትና የውሃ አቅም በሚገባ አላት። እነዚህን አቀናጅቶ በዘላቂነት በመሥራት ድርቅ እየተመላለሰ ሊያደርስ የሚችለውን ችግር መቀነስ ይቻላል።

በሀገሪቱ ለእርሻ ሥራ ሊውል ከሚችለው መሬት ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት እየታረሰ አይደለም። ሀገሪቱ በመኸርም በመስኖም ሊለማ የሚችል መሬት በተለይ በቆላማ አካባቢዎች ላይ በስፋት አላት፤ ለእርሻ ሥራ ከዋለው መሬትም የሚገኘው ምርት ሲታሰብም የሚጠበቀውን ያህል አይደለም።

ለመስኖ ልማት ሊውሉ የሚችሉ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች፣ ሐይቆችና የከርሰ ምድር ውሃ ባለጸጋም ናት። ሰፊ የክረምት ወቅት ያላት እንደመሆኑም በቂ የዝናብ ውሃም አላት።

በሰው ሀብት በኩልም በግብርና ሥራው ላይ ካለው ማኅበረሰብ በተጨማሪ ሰፊ ወጣት አላት።

ሥራ ያለው ከተማ ብቻ አድርገው እየተመለከቱ ወደ ከተማ እየፈለሱ ያሉ ብዙዎች ናቸው። ይህ ሁኔታ መቀየር አለበት። ድርቅ የሚያስከትለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የሚከናወኑ የተለያዩ ተግባሮች እንዳሉ ሆነው ሀገሪቱ ያላትን ሰፊ መሬት፣ የሰው ሀብትና ውሃ አቀናጅቶ መሥራት ላይ ማተኮር ይገባል።

ሀገሪቱ ሊታረስ የሚችል በቂ መሬት፣ ለመስኖ አገልግሎት ሊውሉ የሚችል በቂ የውሃ ሀብትና በቂ የሰው ኃይል አላት ማለቱ ብቻውን የትም አያደርስም። እነዚህ ሀብቶች ዜጎችን ድርቅ ከሚያደርሰው ጉዳት እንዲታደጉ ከዚያም አልፎ የሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት ምሰሶ መሆን እንዲችሉ አድርጎ መሥራት ያስፈልጋል። ወጣቶቹን በማሰልጠን፣ መሬት በማዘጋጀት በዘመናዊ ግብርና ሊሠማሩ የሚችሉበትን ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል።

ይህን ማድረግ እንደሚቻል በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት የተከናወነው ተግባርና የተገኘው ውጤት ሁነኛ ማሳያ ነው። ሀገሪቱ ስንዴ በበጋ ማምረት ችላለች። የማምረት አቅሙም በየዓመቱ እየጨመረ ነው። ልማቱ የተካሄደው በመኸርና በበልግ ወቅት ሥራ ላይ በሚውለው ማሳ ላይ ነው።

ሀገሪቱ በግብርናው መስክ ለውጥ ያሳየችው በትንሽ ቦታ፣ የውሃ አቅምና የሰው ኃይል ላይ በመሥራት ነው። ይህን ልማት በሀገሪቱ ድንግል መሬቶች ላይ ማካሄድ ቢቻል ውጤታማነቱም እጥፍ ድርብ ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም። ይህ ሲሆን ድርቅ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በዘላቂነት መቋቋም ይቻላል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የተማሪዎች መጽሐፍት ጉዳይ!

ኃይለማርያም ወንድሙ

በቅርቡ ትምህርት ሚኒስቴር የ12ኛ ክፍልን ብሔራዊ መልቀቂያ ውጤትን አስመልክቶ የሰጠው መግለጫ የብዙዎች መነጋገሪያ ሆኖ ነበር:: የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በ2014 ዓ.ም የብሔራዊ ፈተና የተመዘገበውን ውጤት ‹‹አስደንጋጭ››ያሉት ከተፈተኑት ተማሪዎችና ከተገኘው ውጤት ጋር በማነፃፀር ነው:: ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተናውን ከወሰዱት ከ980 ሺህ በላይ ተማሪዎች መካከል ወደ 30 ሺህ የሚጠጉት ብቻ ነበሩ ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ማግኘት የቻሉት።

በርግጥ ውጤቱ አስደማሚም አሳማሚም ቢሆንም ግን በኩረጃ ላይ የተወሰደ ‹‹ወሳኝ›› እርምጃ ነው ያስብላል:: እናም ኩረጃ መቀመቅ ወርዶ ሲቀበር የትምህርት ጥራት ብቅ ብቅ ማለቱና ማፍራቱ ይጠበቃል:: መንግሥት በ2011 ዓ.ም አዲስ የትምህርት ፖሊሲ ለማውጣት ከሚያደርገው ጥረት ጎን ለጎን ተማሪዎች እስከ 10ኛ ክፍል የሚማሩበት ሂደት ተለውጦ እስከ 12ኛ ክፍል እንዲሆን ተደርጓል:: የትምህርት ሚኒስቴርም የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ክለሳ በማድረግ በሙሉ እና በሙከራ ትግበራ ላይ ይገኛል::

ባለፈው የካቲት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ወስደው ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 273 ተማሪዎች የላፕቶፕ ሽልማት ያበረከተ ሲሆን መንግሥት ለተማሪዎቹ በዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ የነፃ ትምህርት ዕድል (ስኮላርሺፕ) ማመቻቸቱንም አሳውቋል። በርካታ ተማሪዎችን ያሳለፉ 20 ትምህርት ቤቶችም የዕውቅና ሰርተፊኬት እና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝተው ለተማሪዎቹ ዕውቅና የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች የተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶች መንግሥት ሙሉ ስኮላርሺፕ መስጠቱን አስታውቀዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለተማሪዎቹ ‹‹እንኳን ደስ አላችሁ›› ካሉ በኋላ፣ የተሰጣቸውን ፈተና በአግባቡ መሥራት በመቻላቸው ‹‹ኢትዮጵያን የሚያግዙ 273 ተማሪዎች ተገኝተዋል በዚህም ደስታ ይሰማናል›› ብለዋል:: ተማሪዎቹ እጅግ ዘመናዊ በሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን እንደሚከታተሉና ለኢትዮጵያ እና አፍሪካ የሚደርሱ እንዲሆኑም ጥሪ አቅርበዋል:: ተማሪዎቹ በርትተው ተምረው ሀገራቸውን ሳይረሱ የሚጠቅሙ እንዲሆኑም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሳስበዋል።

በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ወስደው ከ50 በመቶ በታች ውጤት ያስመዘገቡ 106 ሺህ ተማሪዎችም ለአራት ወራት ያህል በሀገሪቱ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በሚሰጠው የአቅም ማሻሻያ (ሪሜዲያል) ፕሮግራም ይሳተፋሉ:: የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራሙ ከአዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በስተቀር በሁሉም የመንግሥት እና የግል ዩኒቨርሲቲዎች ይሰጣል::

ከላይ ያነሳናቸው ነጥቦች በትምህርት ላይ እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎች ተስፋ ሰጪ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው:: ነገር ግን በያዝነው ዓመት በተቀረጸ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የክልል ትምህርት ቢሮዎች መጽሐፍትን አሳትመው ለተማሪዎች በቅጡ ማዳረስ አልቻሉም:: ወታደር ያለ ጦር መሣሪያ ወደ ውጊያ አይሄድም:: ተማሪዎችና መምህራን ያለ መማሪያና አጋዥ መጽሐፍት ወደ ትምህርት ቤት ከሔዱ ትምህርቱ ውጤታማ ይሆናል ተብሎ አይታመንም:: ተማሪዎች ለማጥናትና በመጽሐፍቱ ታግዘው የቤት ሥራ ለመሥራት ይቸገራሉ::

የተለያዩ እንቅፋቶች ቢኖሩም ትምህርት ቢሮዎች ለአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ የሚረዱ መጽሐፍት በፍጥነት ለተማሪዎችና ለመምህራን የሚደርሱበት መንገድ ማመቻቸት ነበረባቸው:: የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ እንዲኖር ከታሰበ መጻሕፍትን በወቅቱና በአግባቡ ለተማሪና አስተማሪ ማድረስ የግድ ይሆናል:: ያለበለዚያ ተማሪው እንደነገሩ ትምህርት ቤት ውሎ መጣ ማለት ብቻ ነው የሚሆነው:: መጻሕፍቱ ለጊዜው በሀገር ውስጥ ማተሚያ በፍጥነት ታትሞ ለተማሪዎች መድረስ ሲገባው፣ ጥራት ላለው ሕትመት በሚል የውጭ ሀገር ማተሚያ ቤት ሲመረጥ መጻሕፍቱ ሳይደርስ የትምህርት ዘመኑም ሲጋመስ ሲታይ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል::

እናም አሁን ባለው ሁኔታ ብዙ ተማሪዎቹ ያለመጽሐፍት እንዲማሩ ተገደዋል:: መጽሐፍቱን ለተማሪዎች ማዳረስ ካልተቻለ ተማሪዎች ከትምህርት መልስ ለማጥናት ይቸገራሉ:: መምህራኑም የሚያስተምሩበት መጽሐፍት እጃቸው ላይ ከሌለ ተማሪዎችን ለማስተማር መቸገራቸው አይቀርም:: የክፍል ሥራና የቤት ሥራ ሲሰጥ የትምህርት መጽሐፍት ካሉ የመማር ማስተማሩ ይቀላጠፋል:: ከሌሉ ግን ይደናቀፋል:: እንኳን ተማሪዎቹ መምህራኑ በትጋት ለማስተማር፣ ለማስረዳትና ጥያቄ ለመመለስ መሰናከል ያጋጥማቸዋል::

ለአብነት ያህል የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በያዝነው ዓመት የተወሰኑ የትምህርት መጽሐፍት ለተማሪዎች ስላልሰጠ ተማሪዎች ደብተራቸውን ብቻ ይዘው ለመሔድ ተገደዋል:: ወላጆቻቸው እና ታላላቆቻቸው እንዲሁም ጎረቤቶቻቸው ሊያስጠኗቸው የሚችሉበት መጽሐፍት ባለመኖሩ ማስጠናት አልቻሉም:: እንዲያውም በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች፤ መምህራኑ የትምህርት መጽሐፍቱ በየምዕራፉ በቴሌግራም እየተላከላቸው ነው የሚያስጠኑት::

‹‹የትምህርት መጽሐፍቱን በቴሌግራም ውሰዱ›› የሚል ‹‹ቀጭን መመሪያ›› ለተማሪዎች የሰጡ መምህራንም እንዳሉ ሰምቻለሁ:: የኪስ ስልክ የሌለውስ ምን ይሁን? ለነገሩ መምህሩ ከመቸገሩ የተነሳ የመጣለት መፍትሔ ይመስለኛል:: ይሁንና ቀኑ እየገፋ ብዙ ተማሪዎች የዘንድሮውን የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት ያለ መጽሐፍት ገፍተውታል::

በኦሮሚያም ክልል ተመሳሳይ ችግሮች እንዳሉ ሰሞኑን በጋዜጣችን የወጣ ዜና ያስረዳል:: በኦሮሚያ ከሚያስፈልጉት 25 ሚሊዮን መጽሐፍት የታተመው ሰባት ሚሊዮን ብቻ ነው:: ከዕቅዱ አንፃር ቢያንስ ግማሹ አልታተመም ማለት አፈጻጸሙ ችግር እንዳለበት ያሳያል::

ያልታተመውን ትተን የታተመው እንኳ ለተማሪዎቹ በሙሉ አለመሠራጨቱ ጉዳዩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ጉልህ ችግር እንደሚፈጥር ያሳያል:: የክልሉ የ2ኛ፣ የ4ኛ እና የ6ኛ ክፍል መጽሐፍት ሕትመት ለቀጣዩ ዓመት ተሸጋግሯል::

የ1ኛ የ3ኛ እና የ5ኛ ክፍል መጽሐፍትንም በተዘጋጀው ዕቅድ አማካኝነት ሥራ ላይ ለማዋል ታስቦ ማድረስ አልተቻለም:: በክልሉ ከ550 ሺህ በላይ የስምንተኛ ክፍል ተፈታኝ ተማሪዎች ስላሉ የ8ኛ ክፍል የአዲሱ ካሪኩለም መጽሐፍ ቅድሚያ ሰጥቶ ለማሰራጨት ተችሏል::

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ መጽሐፍቱን ለማሳተም 6 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በጀት ይጠይቅ እንደነበር የተናገሩት የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ ቢሮው የተጠየቀውን በጀት በወቅቱ አግኝቶ ነበር ይላሉ:: ይሁንና መጽሐፍቱን በሀገር ውስጥ ለማሳተም በክልሉ የሚገኙ ማተሚያ ቤቶች የአቅም፣ የጥራትና የፍጥነት ሁኔታቸው ሕትመቱን ለማከናወን የሚያስችል ባለመሆኑ በሕንድ አገር እንዲታተም መደረጉን ጠቁመዋል::

በውጪ ሀገር መታተሙ ጥራቱንና ፍጥነቱን ለመጨመር ያስችላል የሚሉት የትምህርት ቢሮ ኃላፊው፤ የሕትመት ዋጋ ከሀገር ውስጥ ይልቅ የውጭ ሀገሩ ይቀንሳል:: ይሁንና የማጓጓዣ ወጪው በራሱ ከፍተኛ በመሆኑ በወቅቱ ማስገባት አልተቻለም ሲሉ ተናግረዋል::

የሕንድ የሕትመት ዋጋ በኢትዮጵያ ካለው የቀነሰ መሆኑን እንደ መፍትሔ ብንቀበለው፤ የማጓጓዣ ወጪው ከፍተኛ መሆን ለመጽሐፍቱ አለመድረስ መንስኤ የሆነ ይመስላል:: እናም የትምህርት ቢሮው መጽሐፍቱ አሳትሞ ለማሠራጨት የሄደበት መንገድ ችግሩን ሙሉለሙሉ የሚፈታ አይደለም ማለት ነው::

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርቱ ሥርዓት ለማሻሻል ተስፋ ሰጪ እርምጃዎች እየወሰደ ነው:: የታመመውን ትምህርት እያሳከመው ነው:: ነገር ግን ትምህርት ቢሮዎች በዚሁ ፍጥነትና ህሳቤ ካልሄዱ የሚፈለገውና የጋራ ግብ የሆነውን የትምህርት ጥራት ማስጠበቁ አዳጋች ይሆናል:: ስለሆነም ለቀሪው አጋማሽ የትምህርት ጊዜ መጽሐፍቱ ለተማሪዎች ተዳርሰው ጥራት ያለው ትምህርት እንዲማሩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በጋራ ሊሠሩ ይገባል::

# ነፃ ሃሳብ

## «የሽግግር ፍትሕ“ ተግባራዊ ሲሆን የደፈረሰው ይጠራ ይሆን?

**ዳግም ከበደ**

በሽግግር ወቅት አገር ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ይፈታተኗታል።ግጭት፣ አለመግባባት፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ሙስናና አለመስከን ተደራርበው ዜጎችን እረፍት ይነሱታል። የጠራው እስኪሰክን፣ የጎደለው እስኪሞላ፣ የበደለው እስኪክስና እውነት ከፍትሕ ጋር እስኪታረቅ ብዙ ውጥንቅጦች ዙሪያዋን ይከቧታል።

“ግርግር ለሌባ ይመቻል” እንዲሉ በዚህ መሐል እዚህም እዚያም ግጭትና ዝርፊያን ምግባራቸው ያደረጉ ቡድኖች አጋጣሚውን መጠቀማቸው የማይቀር ይሆናል። ወንጀላቸውን ለመሸሸግ እላይ እታች የሚሉ ግለሰቦችም እንደዛው።

ኢትዮጵያ ላለፉት አምስትና ከዚያ በላይ ዓመታት ሀገርን አደጋ ላይ ጥለው የነበሩ አለመግባባቶችን አስተናግዳለች። ሉዓላዊነትን ፈተና ውስጥ የከተቱ አለመግባባቶች ተከስተዋል። በልዩ ልዩ አካባቢዎች ግጭቶች ተከስተው ዜጎች ለሞት፣ ለመፈናቀል እና ቤት ንብረታቸውን እስከማጣት ደርሰዋል።

በሰሜኑ ክፍል ለሁለት ዓመታት ያህል የዘለቀው ጦርነት አያሌ ዜጎችን የምድር ከርስ ውስጥ ከመክተት አልፎ በምጣኔ ሃብት፣ ማኅበራዊ ጉስቁልናና ለከፋ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ምክንያት ሆኖ አልፏል። ከዚያ ባለፈ ከታሪክ፣ ከወሰን፣ ከቆየ ቁስል፣ ከሕግ የበላይነት፣ ከጋራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ወዘተርፈ ጋር በተያያዘ ሰፊ የአመለካከት ልዩነቶች የተስተናገዱበትና ሀገርን በስጋት እንደ ቆዳ የወጠሩበት ወቅት ነው።

ከላይ ካነሳነው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያይዞ መንግሥት በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች የተከሰቱ አለመግባባቶች፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ የቆየ ቁርሾና በዘመን ሂደት ውስጥ የተከሰቱ ልዩነቶችን በሰከነ መንገድ ለመፍታት ሁነኛው መፍትሔ “የሽግግር ፍትሕ” መሆኑን አምኖ ለመፍትሔው እየሠራ መሆኑንና ቁርጠኝነቱን እያሳየ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ እየገለፀ ይገኛል።

በዋናነት በኢትዮጵያም ሆነ በመሰል ሀገራት ከግጭቶች በኋላ ሰላማዊ ሁኔታዎችን ለመፈጠር ሲሞከር ትልቅ ርዕሰ-ጉዳይ ሆኖ እንደ ዘላቂ የግጭት ማቆሚያ መንገድ የሚወሰደው “ያጋጠሙ የመብት ጥሰቶች እና ወንጀሎች በምን መልኩ ምላሽ ይሰጣቸው?” የሚለው ጉዳይ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዘመናት ሲከሰት በቆዩ አለመግባባቶች ውስጥ ይህ ጉዳይ ዋንኛ የውይይት ርዕስ ነው። ምሑራንን እና የፖለቲካ ቡድኖችን አተካራ ውስጥ የሚከተው አጀንዳም ይሄው ነው።

የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት በተንሰራፋበት፣ ዜጎች ላይ ከፍተኛ የሞራልና የምጣኔ ሃብት ድቀት በተፈጠረበት፣ ሰፊ የአመለካከት ክፍተት ባለበት እና ፅንፍ የያዙና የማይታረቁ የሚመስሉ ሃሳቦች በበዙበት የሽግግር ወቅት “እውነትና ፍትሕን” አዛምዶ የሚይዝ፣ በተለያየ ጎራ የሚገኙ ቡድኖችን በተሻለ መልኩ አስታርቆ ለሀገርና ለዜጎች ደህንነት ሲባል በአንድ ዓላማ የሚያሰልፍ ሁነኛ መፍትሔ “የሽግግር ፍትሕ” እንደሆነ በብዙ የፖለቲካ ልሂቃንና ምሑራን ይታመናል።

ለዚህም ይመስላል ኢትዮጵያ አሁን የገጠማትን እንቅፋት በብልሃት ለማሸነፍና ወደ ሰከነውና ወደ ተረጋጋው ሐዲድ ውስጥ ለመግባት መንግሥትን በበላይነት እየመራ የሚገኘው ብልጽግና ፓርቲ፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎችና ልሂቃን በጋራ እየሠሩ የሚገኙት። ለመሆኑ ይህ አካሄድ የትኛውን መጨረሻ ያሳየን ይሆን?

ጉዳዩን ከስር መሠረቱ ለማጥራት እንዲያስችለንና ፅንሰ-ሀሳቡን መለየት እንድንችል በቅድሚያ “የሽግግር ፍትሕ”ን ምንነትን መረዳት ይኖርብናል።

**የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት በተንሰራፋበት፣ ዜጎች ላይ ከፍተኛ የሞራልና የምጣኔ ሃብት ድቀት በተፈጠረበት፣ ሰፊ የአመለካከት ክፍተት ባለበት እና ፅንፍ የያዙና የማይታረቁ የሚመስሉ ሃሳቦች በበዙበት የሽግግር ወቅት«እውነትና ፍትሕን» አዛምዶ የሚይዝ፣ በተለያየ ጎራ የሚገኙ ቡድኖችን በተሻለ መልኩ አስታርቆ ለሀገርና ለዜጎች ደህንነት ሲባል በአንድ ዓላማ የሚያሰልፍ ሁነኛ መፍትሔ «የሽግግር ፍትሕ» እንደሆነ በብዙ የፖለቲካ ልሂቃንና ምሑራን ይታመናል**

“የሽግግር ወቅት ፍትሕ አስከፊ ግጭት፣ ጭቆና እና የመብት ጥሰትን ተከትሎ ተጠያቂነት፣ ፍትሕ እና እርቅን በማረጋገጥ ዘላቂ ሰላም የሚፍጥሩ ሥራዎችን የሚያጠቃልል ሂደት” መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያሰፍራል።

አንዳንድ ሰዎች ተጠያቂነት የሚያስገኘው ፍትሕ የተሻለ ሰላም ያመጣል ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የሽግግር ወቅት ፍትሕን እንደ አማራጭ ያቀርባሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳለው አለመግባባት ለመሰሉ ጉዳዮችና በልዩ ልዩ ዓለማችን ላይ የሚከሰቱ ግጭቶች የተሻለው አማራጭ የሽግግር ፍትሕ እንደሆነ ይታመናል።

የሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት ከተሰጣቸውና በአግባቡ ተግባራዊ የሚደረጉ ከሆነ ውጤቱ ያማረና ኢትዮጵያን ወደምንፈልገው የሰላም፣ የእድገት፣ የትብብርና አንድነት መንገድ እንደሚወስዳት ማረጋገጥ እንችላለን። ለዚህ ደግሞ የሽግግር ወቅት ፍትሕ ዓላማዎችን መገንዘብ ይኖርብናል።

የመጀመሪያው “እውነትን ፈልጎ ማወቅና በዚያ ዙሪያ መተማመን ላይ መድረስ ነው” በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ለተከሰቱ ችግሮች፣ ለደረሱ ጥፋቶች እውነተኛውን መንስኤና ተጠያቂነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህንን ማድረግ ስንችልና በጠረጴዛው ላይ ለማምጣት ፍቃደኛ ስንሆን ለመፍትሔው አንድ እርምጃ ወደ ፊት እንደሄድን መገንዘብ እንችላለን።

ሁለተኛውና ዋንኛው ጉዳይ ደግሞ “የተጎዱ ሰዎችን መልሶ ማቋቋም ነው” በኢትዮጵያ ውስጥ ከጫፍ እስከጫፍ ባሉ በሮች በተለያዩ ጊዜያት በሚከሰቱ ግጭቶች ምክንያት ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ሃብታቸው ወድሟል። የሞራል ውድቀት ደርሶባቸዋል። ለስነ ልቦና ችግር ተዳርገዋል። ይህንን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ እከሌ ከእከሌ ሳንል ተጎጂዎችን መካስ ይኖርብናል። ይህንን ስናደርግ በእርግጥም የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ እንደሆነ ማረጋገጥ እንችላለን።

ሦስተኛውና መሠረታዊ ጉዳይ “የወንጀል ተጠያቂነት” ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የደረሱ ከፍተኛ ጥፋቶች፤ለደረሰው ንፁሕ የሰው ሕይወት መጥፋት፣ ለንብረት ውድመት ባለቤት እንዳለው ማመን ይገባናል። ግጭት ጠማቂ የነበሩ አካላት ኃላፊነት ወስደው ተጠያቂ ሲሆኑ ፍትሕ መድረሻዋን እንድታገኝ ማድረግ ከቀዳሚ ሥራዎች ውስጥ መግባት ይኖርበታል። አጥፊው ሲጠየቅ በቀጣይ መሰል ተግባሮች ላይ ለመሳተፍ እጁን የሚሰድ ትምህርት የሚወስድበት መልካም አጋጣሚ ይፈጠራል።

የገፈቱ ቀማሽ የሆኑ ዜጎችም “ፍትሕ” እንዳለ እንዲያምኑና በሚመሠረተው ሥርዓት ላይ መተማመንን እንዲያሳድሩ በር ይከፍታል። በጋራ ዳግም ያዘመመውን ምሰሶ መልሶ ለማቆም ይህ እርምጃ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ይህም ሲሆን ሌላኛዎቹ የሽግግር ፍትሕ መሠረታውያን ተሟሉ ማለት ያስችለናል።

አራተኛውና መሠረታዊው የሽግግር ፍትሕ ዓላማ “ሕግ፣ ፖሊሲ” ጨምሮ መሰል ለሀገር ግንባታና ዘላቂ ሰላም እንቅፋት የሆኑ የአሠራር ሥርዓቶችን ለማሻሻል ቁርጠኝነት ማሳየት ነው። ዜጎች በጋራ በአንድ አገር ጥላ ስር እንዲኖሩ ሁሉም የተስማሙበት የሕግ ማዕቀፎች ሊኖራቸው ይገባል።

አንዱን የእናት ልጅ ሌላውን የእንጀራ ልጅ የሚያደርግ ሥርዓት፣ ሕግ፣ ሕገመንግሥትም ሆነ ማንኛውን ማዕቀፍ መሻሻል የጋራ መግባባት ላይ መምጣት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ውይይት ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳል። ኢትዮጵያንና ዜጎቿን ወደፊት አላራምድ ያለና ቀፍድዶ የያዘ ሕግ ካለ በሰከነ ውይይት ሊታይና ዳር ሊይዝ የግድ ነው። ይህን ማድረግ ስንችል መንግሥትም ሆነ ምሑራን እየደከሙለት የሚገኘው የሽግግር ፍትሕ ፈር እንዲይዝ ትልቁን መደላድሉን እንፈጥራለን።

ምሑራን ሁለት ዓይነት የሽግግር ወቅት ፍትሕ እንዳለ ይናገራሉ። የመጀመሪያው የሽግግር ሂደቱ የወንጀል ክስ ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲሄድ የሚያደርግ ነው። ይህንን በእኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈትኑ አያሌ ጉዳዮች መኖራቸው እሙን ነው። ምክንያቱ ደግሞ በብሔርና በጎጥ ለዘመናት ለመከፋፈልና በዚያ ጥላ ውስጥም ተሸሽጎ ከተጠያቂነት ለማምለጥ የሚደረጉ ሙከራዎች አሉ።

ይህ ተግባራዊነቱንና ውጤታማነቱን አደጋ ውስጥ የሚጥል ነው። አንድ የፖለቲካ ቡድን ወይም ግለሰብ ላይ ክስ መሥርቶ ተጠያቂ ለማድረግ ጥረት ቢደረግ በቀጥታ አንዱን ብሔር አሊያም ጎጥ ለማጥቃት እንደተሠራ ደባና ሴራ የማይወሰድበት ምክንያት ስለማይኖር በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊታይ ይገባዋል።

ሌላው የሽግግር ሂደት ውስጥ የሚካተተውና ሁለተኛው የፍትሕ አይነት ምንም አይነት “ክስ እንዳይመሠረት፤ አጥፊዎቹ እንዲለዩና ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ እንዲጠይቁ” የሚያደርግ አካሄድና የሽግግር ፍትሕ አይነት ነው። ይህም አካሄድ የራሱ የሆኑ ክፍተቶች ያሉበት ቢመስልም በመጠኑም ቢሆን ጉዳት የደረሰባቸው አካላት ሕመማቸውና የደረሰባቸው የውስጥ ቁስለት እውቅና እንዲያገኝ የሚያደርግ በመሆኑ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው።

ሆኖም ግን የማይታለፍ ግፍ የሠሩ፣ የሕዝብን ሃብት ዘርፈው ለግል ዓላማቸው ያዋሉ፣ በከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ውስጥ እጃቸው ያለበት ግለሰቦችም ይሁን ቡድኖችን የማምለጫ ቀዳዳ የሚሰጥ ክፍተት ስላለው ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ ነው ማለት ያዳግታል። ይሁን እንጂ ይህ ተግባራዊ ባለመሆኑ ከሚደርስ ቀጣይ ጥፋት ይልቅ ለሀገር መረጋጋትና ሰላም መስፈን በሚኖረው መፍትሔ ብንመርጠው የሚበጅ ነው።

### ማጠቃለያ

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የተለያዩ ሀገራት የሽግግር ወቅት ፍትሕን ተግባራዊ አድርገዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሩዋንዳ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ዩጎዝላቪያ እና ቺሊ ይገኙበታል። የሩዋንዳው የዘር ፍጅት በሽግግር ወቅት ፍትሕ መቋጨቱን ሁላችንም የምናስታውሰው ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ተበዳዮች በደላቸው እንዲታወቅ ተደርጓል።

አጥፊዎችም ለፍርድ ቀርበዋል። ጉዳዩም ለማስተማሪያነት በሙዚየም ጭምር ተቀምጧል። በፊልም በታሪክ መጽሐፍት ጭምር ለሰው ልጆች መማሪያ ነው። ሁላችንም አስከፊ ስለሆኑ የሰብዓዊ ጥሰቶች ምሳሌ እያደረግን ይህን መሰል ጉዳት እንዳይደገም መቀጣጫ እያደረግነው ነው።

የሽግግር ፍትሕ ሂደትን ስናነሳ ደቡብ አፍሪካም ተመሳሳይ እርምጃ ወስዳ እንደነበር ያስታውሰናል። በአፓርታይድ ሥርዓት ብዙ ቁስል ያስተናገደችው ይህቺ ሀገር እንደ ሀገር ምልክት በምታያቸው ኔልሰን ማንዴላ (ማዲባ) መሪነት ዘመናት ያቆሰላትን ችግር መፍትሔ አበጅታለታለች።

ብዙ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ቢነሱበትም የአፓርታይድ ሥርዓት የተቋጨው በእውነት አፈላላጊ እና የእርቅ ኮሚሽን ነው። በዩጎዝላቪያም አጥፊዎች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የቀረቡበትን ሁኔታ ስናስታውስ፣ ይህ አካሄድ ወደ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ መምጣቱን እንድናበረታታ ይገፋፋናል፤ “የሽግግር ፍትሕ እውን ሲሆን የደፈረሰው ይጠራ ይሆን?” ብለን እንድንጠይቅም ያስገድደናል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የዓሣ ልማት - በጋምቤላ ክልል

ወርቅነሽ ደምሰው

**ኢትዮጵያ ሰፊ የዓሣ ሀብት እንዳላት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህን የዓሣ ሀብት በማልማትም ሆነ በመጠቀም ረገድ ግን ብዙም አልተሠራበት። ይህም ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አናሣ መሆኑን ያመለክታል።**

**ልማቱ አለመዘመኑና ሀብቱንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሚካሄድ የተጠናከረ ሥራ አለመኖር የትኩረት ማነስ ማሳያዎች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። በአንድ ወቅት በዓሣ ሀብት ከሚታወቁ የኢትዮጵያ ክፍሎች አንዱ በሆነው ጋምቤላ ክልል ዓሣን አቀነባብሮ ለውጭ ገበያ በማቅረብ በዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት በመንግሥት በኩል አቅጣጫ ተይዞ እንቅስቃሴ ተጀምሮ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ያም ቢሆን ወደ ውጤት ተቀይሮ አልታየም።**

**ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በዚሁ በጋምቤላ ክልል ያለውን እምቅ የዓሳ ሀብት በማልማት ለመጠቀም የሚያስችል ፕሮጀክት ተቀርጾ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ የዓሣ ልማቱን ምርታማነት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማሳደግ ነው። ፕሮጀክቱንም የክልሉ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን በበላይነት እየመራው ይገኛል። እኛም ስለፕሮጀክቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ከክልሉ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ያሲን በላይ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዓምዳችን ይዘን ቀርበናል።**

**አዲስ ዘመን፡- በጋምቤላ ክልል ስላለው የዓሣ ሀብትና ስለፕሮጀክቱ ቢገልጹልን?**

**አቶ ያሲን፡-**በጋምቤላ ክልል ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ይገኛሉ። በእነዚህ ሁሉ የውሃ አካላት ደግሞ ከፍተኛ መጠን ያለው የዓሳ ሀብት አለ። በውሃ አካላቱ ውስጥ ወደ 138 አይነት የዓሣ ዝርያዎች እንደሚገኙ ከዚህ ቀደም የተደረጉ የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ። አሁን ግን አዳዲስ ዝርያዎች ሊገኙ እንደሚችሉ፣ ከነባሮቹ መካከል ዝርያቸው የጠፋ ሊኖር እንደሚችልም ይገመታል። ክልሉ በሀገር ደረጃም በዓሣ ሀብት ከፍተኛ አቅም አለው ተብሎ እውቅና ተሰጥቶታል።

በመተግበር ላይ የሚገኘው ፕሮጀክት ተለምዳዊ (ባሕላዊ) በሆነ መንገድ የሚካሄደውን የዓሣ ልማት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመተካት ልማቱን ማሣደግ ነው። የምርት ማሳደጉ ሥራ ወደ ውጪ በመላክ በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ በሚል የጋራ አስተሳሰብ ተይዞ የተጀመረ ነው። ፕሮጀክቱን ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የክልሉ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን በጋራ እያከናወኑት ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ፕሮጀክቱ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ያሲን፡-** በፕሮጀክቱ ዓሣን ለማምረት ሥራ ስድስት ቦታዎች/ ሳይቶች/ በጥናት ተለይተዋል፤ ከስድስቱ ሳይቶች በ2013 መጨረሻ በ2014 መጀመሪያ ሦስት ፓይለት ፕሮጀክቶች ተለይተዋል። እነዚህም አበቦ ወረዳ ፣ጋምቤላ ከተማ እና ኢታንግ ወረዳ ናቸው። ጋምቤላ ከተማ ከሌሎቹ በተሻለ ከፍተኛ መጠን ያለው ዓሣ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜም በነዚህ አካባቢዎች የሚለማውን ዓሣ ደህንነቱ ተጠብቆ ለአካባቢው ማኅበረሰብና አዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ ዓለም አቀፍ ሆቴሎች ለማቅረብ እቅድ ተይዞል። ጋምቤላ ያለው ማጠራቀሚያ ማዕከል ለስድስቱም ሳይቶች ማሰባሰቢያ ማዕከል አለው፤ እንደ ሌሎቹ ደግሞ የራሱ የሆነ በአንድ መስኮት ጤንነቱ የተጠበቀ ዓሣ የሚሸጥበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በፕሮጀክቱ ምን አይነት ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ታስቧል?**

**አቶ ያሲን፡-**ፕሮጀክቱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ በአፍሪካ አምስተኛ ደረጃ ላይ ያለ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይጠቀማል። ዓሣ ማስገሪያ ጀልባዎቹ ዘመናዊ ናቸው። ይህ ፕሮጀክት ከመከፈቱ በፊት ወጣቶች ዓሣ ለማስገር የሚጠቀሙት በእንጨት ጀልባ ነበር። ጀልባው እንዲንቀሳቀስ የሚደረገው በሞተር ነበር፤ አሁን ሞተሩ በነዳጅ ሳይሆን በፀሐይ ኃይል ወይም በኤሌክትሪክ ቻርጅ የሚንቀሳቀስ እንዲሆን ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት ነዳጅ ከሆነ እየተንጠባጠበ ውሃ ሊበክል ስለሚችል ነው፤ ጤንነቱ የተጠበቀ ስንል ውሃ ውስጥ ያለው ዓሣ በሚንጠባጠበው ነዳጅ ችግር እንዳይገጥመው ለማድረግ ነው። በሌላ በኩል ውሃው ሊበከል ይችላል፤ ይህ ማለት ኅብረተሰቡ ሌላ አገልግሎት ሊጠቀም የሚችለውን ውሃም ይበከላል ማለት ነው።

ዓሣ አስጋሪዎቹ አሁን ዓሣውን የሚያቀርቡት እንደፊቱ በተለምዷዊ እቃ አይደለም፤ ማቀዝቀዣ(Ice box) ውስጥ አርገው መሆን አለበት። ሁሉም የማከማቻ ማዕከላት በረዶ ያመርታሉ። ዓሣውን አስግረው ሲጨርሱ ማቀዝቀዣው (Icebox) ውስጥ ያስቀምጡና ወደ ማከማቻ ማዕከሉ ያመጣሉ።

ማከማቻ ማዕከሉ ሦስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው መቀበያውና ፕሮሰስ የሚያደርጉ (ሥልጠና የተሰጣቸው ዓሣን ፕሮሰስ የማድረግ ልምድ ያላቸው) ሠራተኞች ያሉበት ክፍል ነው። ዓሣው ፕሮሰስ ከተደረገ በኋላ ወደ ሚቀጥለው ክፍል ይገባል፤ ይታሸግና ማቀዝቀዣ ( ፍሪጅ) ውስጥ ይቀመጣል።

ከጋምቤላ ክልል ወደ አዲስ አበባ እስኪላክ ድረስ ራሱን የቻለ አንድ ትልቅ ማከማቻ አለው። ማቀዝቀዣ (ፍሪጅ) ሲባል በተለምዶ በየቤታችንን የምንጠቀመው አይነት አይደለም። ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተገጠመለት በአይነቱ ለየት ያለ ነው። ዓሣ በጣም በቀላሉ ሊበላሽ የሚችልበት ሁኔታ አለ፤ አሁን ሥራ ላይ የዋለው ማቀዝቀዣ ዓሣው የተፈለገውን ያህል ጊዜ ቢቆይ እንዳይበላሽ ማድረግ የሚያስችል ቴክኖሎጂ የተገጠመለት ነው። መብራት እንኳን ቢጠፋ የራሱ የሆነ አውቶማቲክ ጀነሬተር ያለው ነው፤ ወዲያውኑ ራሱ የሚያበራ መብራቱ ሲጠፋ ደግሞ ራሱ የሚያጠፋ ቴክኖሎጂ የተገጠመለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ከአበቦ ወረዳ እና ከኢታንግ ወረዳ እንዲሁም ሌሎች ሳይቶች ሲገነቡ ከእነዚያ ሳይቶች ዓሣዎችን የሚያመጡ የራሳቸው ማቀዝቀዣ ክፍል የተገጠመላቸው ባጃጆች አሉ። ስለዚህ ከሳይቶቹ ወደዋናው ማዕከል ስናመጣ ዓሣው በአየር ሁኔታ ወይም በሌላ ምክንያት ይበላሻል የሚል ስጋት አይኖርም።

**አዲስ ዘመን፡- ፕሮጀክቱ ከተመረቀ በኋላ ምን ዓይነት ተግባራት እያከናወነ ይገኛል?**

**አቶ ያሲን፡-** አሁን ወጣቶችን በማኅበር እያደራጀን ነው። አስጋሪዎች የራሳቸው ማኅበር አላቸው። የሚያቀናብሩትም /ፕሮሰስ የሚያደርጉትም/ የራሳቸው ማኅበር አላቸው፣ መረብ የሚሠሩ ወጣቶችም እንዲሁ ማኅበር አላቸው። በሦስቱም ሳይቶች እነዚህን ወጣቶች እያደራጀን እንገኛለን።

አሁን ሥራ ያልተጀመረበት ዋና ምክንያት ወጣቶቹ ዓሣውን ለማስገር የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ዘመናዊ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ግንዛቤ ብቻ ሳይሆን እውቀትም ስለሚያስፈልግ ነው። በየሳይቱ ምርጫው ተካሄዷል። ፕሮሰስ የሚያደርጉ፣አስጋሪዎችና መረብ የሚሠሩ ወጣቶች ተለይተዋል። አንደኛ በማኅበራት ማደራጃ መስፈርት መሠረት እያንዳንዱ ማኅበር ስታንደርዱን የጠበቀ ማኅበር እንዲሆን ይደረጋል። ሁለተኛ ለእነዚህ ዘመናዊ ማሽኖች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ስለሚያስፈልግ ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል።

በሦስቱ ሳይቶች መጀመሪያ ፕሮጀክቱን ሥራ ለማስጀመር ለ550 ወጣቶች የሥራ እድል ይፈጠራል። እነዚህ ወጣቶች በማኅበር ተደራጅተው ሕጋዊ ሆነው የሚገቡ ናቸው። ሆኖም ግን ማንኛውም ሰው በግሉ ዓሣ አስግሮ እዚያ አምጥቶ መሸጥ ይችላል። ዓሣው ጤንነቱ የተጠበቀ መሆኑና ትክክለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ይወሰዳል፤ በተቀመጠው አሠራር ውስጥ አልፎ ለሽያጭ ይቀርባል።

ሁሉም በጥናት የተካተቱት ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ሲገቡ ደግሞ ሰነዱ ላይ እንደተቀመጠ በመደበኛ በማኅበር ለሚደራጁና በግላቸው ለሚያሰግሩ አምስት ሺ ሰዎች የሥራ እድል ይፈጥራል ይላል። አሁን ላይ ለዓሣ አስጋሪዎች፣ ለፕሮሰሰሮች እና ለመረብ ሠሪዎች ለእያንዳንዱቸው ራሱን የቻለ የአንድ ሳምንት ስልጠና 70 በመቶ በተግባር እና 30 በመቶ በንድፈ ሀሳብ/ቲዎሪ/ ሥልጠና ከሰጠን በኋላ እውቅና ያለው ሥራ ይጀመራሉ። አሁን ማሽኖችን ለመጠቀም ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ፕሮጀክቱ በዓመት ምን ያህል ዓሣ ማምረት ይችላል?**

**አቶ ያሲን፡-** አሁን በዓመት 25 ቶን ዓሣ ሊያመርት



ምክትል ኮሚሽነር ያሲን በላይ

እንደሚችል ይገመታል። ገና ጅማሮ ስለሆነ በጠበቅነው ልክ ላይገኝ ይችላል። ነገር ግን ከፍተኛ ድርሻ ያለው ነው ብለን እንወስዳለን። የዓሣ ምርቱ እየጨመረ እንደሚሄድ ምንም ጥርጥር የለውም። ሰው እየለመደው ሲሄድ ፍላጎቱም እየጨመረ ሲመጣ የዓሣ መጠኑ ከፍተኛ ስለሆነ ምርቱም እየጨመረ እንደሚመጣ ምንም አያጠያይቅም።

በምርቃት ወቅት የተወሰኑ ወጣቶች ለአምስት ቀናት ሥልጠና እንዲወስዱ በመደረጉ ዓሣ ከማስገር ጀምሮ ሁሉንም ሂደቶች በተግባር ያሳዩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በዚህ ወቅት ጋምቤላ ክልል ጉር የሚባል ዓሣ አለ፤ ይህን ዓሣ ወጣቶች ናቸው ያመጡት። አንዱ 160 እስከ 170 ኪሎግራም የሚመዝን በመሆኑ በዕለቱ የተገኙ ሰዎች በእጅጉ ተገርመውበታል። ይህን ዓሣ ሁለት ሰዎች በእንጨት ተሸክመው ነው ያመጡት። የዓሣ ገበያውም ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ይታወቃል። በዓሣ ማስገር ላይ የሚሠማሩ ወጣቶች ያላቸውን አቅም አሟጠው ሊጠቀሙ እንደሚገባ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን የተፈጠረው የገበያ ትስስር ምን ይመስላል?**

**አቶ ያሲን፡-**የገበያ ችግር ያጋጥመናል ብለን አናስብም። ጉዳዩን በተለያዩ ዜናዎች የሰሙ አካላት ዓሣውን ወደ አዲስ አበባ ለመላክ የጋራ አሠራር እንፍጠር እያሉ ነው። በዘርፉ ለመሠማራት የሚፈልጉ አካላት በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ የሚጠይቁ ሰዎች አሉ።

ሁሉም ሳይቶች ሥራ ጀምረው የማመላለሻ መኪናዎች ተገዝተው ወደ ሥራ እስከሚገቡ ድረስ የአቅም ውስንነት ሊኖር ስለሚችል የገበያ ትስስሩን ሊፈጥሩ የሚችሉ ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ባለሀብቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ በጋራ መሥራት የሚያስችል አማራጭ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- ፕሮጀክቱ ወደ ሥራ ከገባ በኋላ ምን ይጠበቃል ?**

**አቶ ያሲን፡-** እነዚህን የፕሮጀክት ሳይቶች ስናጠናቅቅ ሦስት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ። የመጀመሪያው ለወጣቶች የሥራ እድል መፍጠር ነው። የጋምቤላ ወጣቶች ከልጅነታቸው ጀምሮ ዓሣ ማስገር ባሕላቸው ነው። ሁለተኛው አዲስ አበባ ያሉ ዓለም አቀፍ ሆቴሎች በምንም አይነት መመዘኛ ቢታይ ጋምቤላ ካለው ዓሣ የማይበልጥ ዓሣ በውጭ ምንዛሪ ያስገባሉ። ይህንን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት ነው። የሀገራችን ምርት የሆነውን ዓሣ ለእነዚህ ሆቴሎች ማቅረብ ከቻልን የውጭ ምንዛሪ እንዲቀር ማድረግ እንችላለን።

ሦስተኛው የጋምቤላ የመሬት አቀማመጥ በጣም አመቺ ነው። ሜዳ ነው፤ ወጣ ውረድ የለውም። ስለዚህ ግራና ቀኝ ግንባታ በማካሄድ የዓሳ መጠንን መጨመር ይቻላል። ይህንን የምናደርገው ለሀገራችን ሆቴሎች ዓሣ ለማቅረብ ብቻ አይደለም፤ ወደ ውጪ በመላክም የውጭ ምንዛሪ በማግኘት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ድርሻውን የሚወጣ ሀብት አድርገን ለመጠቀም እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ፕሮጀክቱ የሚጠቀመው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንደመሆኑ መጠን እነዚህ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወደሥራ በማስገባት ረገድ ምን ታስቧል?**

**አቶ ያሲን፡-** የዘመናዊ ማሽን ኦፕሬሽን እክል ሊያጋጥም ይችላል። ምክንያቱም አሁን የሚሰጠው ሥልጠና በጥልቀት የሚሰጥ አይደለም፤ ለጥቂት ቀናት ነው የሚሰጠው። ጊዜ ከማጠሩና ከመሣሪያዎቹ አዲስነት አንጻር የተወሰኑ ክፍተቶች ሊያጋጥሙን ይችላሉ፤ የሥልጠናው ጊዜ ውስን ስለሆነ ማሽኑን ኦፕሬት ሲያደርጉ የተወሰነ ችግር ሊያጋጥም ይቻላል። የጎላ ችግር እንዳይገጥም በሚል ወጣቶቹ ሥልጠና ሳይሰጣቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ አይደረግም።

አንደኛው የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ብቻ በትምህርት ደረጃቸውም ከዚያ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጣቶችን እናካትታለን የሚል ሀሳብ አለን። ሁለተኛው ማሽኖችን ያስገባው አካል ተበላሸ ሲባል ለመጠገን ወይም ለማስተካከል ቃል የገባ ስለሆነ ያግዘናል የሚል እምነት አለ።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻም ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለዎት?**

**አቶ ያሲን፡-** የጋምቤላ የዓሣ አቅም ዛሬ የተፈጠረ ሳይሆን የቆየ ነው። እስካሁን በአቅም ውስንነት የተነሳ ሳናስተዋውቀው በመቆየታችን ሀብት ባክኗል። ይህን ሀብት አልምቶ በመጠቀም በኩል አሁን በጣም ከፍተኛ ፍላጎት አለ። ፍላጎቱ በጨመረ ቁጥር የገበያ ትስስሩ እየሰፋ ይሄዳል። በዘርፉ የሚሠማሩ ወጣቶች ከፍተኛ የኢኮኖሚ መሠረት ያገኛሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። የዓሣ ሀብቱ በክልልና በሀገር ደረጃ ለኢኮኖሚው የበኩሉን ሚና ሊያበረክት የሚችል ስለሆነ አቅምና ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ቢደግፉ እኛም፣ ማኅበሩም፣ ክልሉም፣ ሀገርም ተጠቃሚ መሆን እንችላለን የሚሉ ግለሰቦች ካሉ ከኛ ጋር አብረው እንዲሠሩ ጥሪ አቀርባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ሳደረጉልን ትብብር አመሰግናለሁ።**

**አቶ ያሲን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## ኑሮ ንሯል፤ መፍትሔውስ ?

ግርማ መንግሥቴ

**ነጋዴው ሕገ ወጥ በሆነ ንግድ ላይ መሠማራት የለበትም፤ አላስፈላጊና ምስጢራዊ ክምችትን በመፍጠር የግብይት ሥርዓቱን በግል ጥቅም በመለወጥ አላስፈላጊ መጨናነቅንና ትርምስን በሀገር ላይ መፍጠር አይገባውም። ይህ ሄዶ ሄዶ ራሱን የንግዱን ማኅበረሰብ ነው የሚጎዳው። በርካታ ነገሮችንም ያሳጣል**

የኑሮን ነገር "ኑሮ ንሯል" የሚለው አይገልፀውም። አይደለም ኑሮ ንሯል፣ "ኑሮ ጦዟል"ም የሚገልፀው ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዐይን ጭፍን-ክፍት ፍጥነት ተለዋዋጭ የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን፤ ገበያው ከገበያ ሥርዓት ማፈንገጡም ሌላው ነው።

እንኳን ዘንቦብሽ . . . እንዲሉ፣ ድሮም ባልጠና ኢኮኖሚ ላይ የገበያ አሻጥር ተሠርቶበት፣ በአሻጥሩም ውስጥ አሻጥረኛ ተሰግስጎበት፣ የንግድ ሥርዓቱ በደላላ ተዘውሮ፣ ጎማው በኪራይ ሰብሳቢ ተሽከርክሮ . . . ይቅርና፣ እንኳን . . . እንዲሁም አልቅስ አልቅስ ይለኛል እንደሚባለው፣ ድሮውንም በከፍ-ዝቅታ የታጀበ ኢኮኖሚ እንዲህ እንደ አሁኑ ዓይነት ፈተና ሲገጥመው የሸማቹ የመግዛት አቅም "ወገቤን" ቢል የሚፈረድበት አይሆንም።

አሁን ባለው ሁኔታ ገበያና ግብይት ከሸማች ዜጎች ቁጥጥር ውጭ ሆነዋል። የጠዋቱ ለማታ፣ የማታው ለጠዋት . . . ባለበት አይገኝም። ገንዘቡ "የመግዛት አቅሜን ተነጥቂያለሁ" ካለ ቆየ። ሁኔታው ሁሉ አስደንጋጭ ነው። ጀግና ካልመለሰው መሸምጠጡ ነው። እንደ አንዳንድ የችግሩ ገፈት ቀማሽ ሀገራት፣ ሳሙና ለመግዛት ብር በጆንያ ሞልተን በጋሪ እየገፋን ላለመሄዳችን ምንም ዋስትና የለንም። በዋናነት የዚህ ሁሉ ምክንያት ደግሞ ገበያው ባለቤት ማጣቱ ሲሆን፤ ገሳጭም ገልማጭም የለውም። በመሆኑም እንዳሻው ሲፈነጭ ውሎ፣ እንዳሻው ሲፈነጭ ያድራል። (የቤት ኪራይ በሚያስደነግጥ ሁኔታ እየጨመረ ስለ መሄዱም ይኸው የገበያው እብደት ያመጣው ጦስ መሆኑንም ልብ ይሏል።)

የውጭ ምንዛሪ፣ የነዳጅ ዋጋ መናር፣ ጥቁር ገበያ፣ የፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም፣ የቁጥጥር መላላት (ወይም አለመኖር)፣ በንግዱ ዓለም የተሠማራው ባለ ሀብት ይሉኝታ ማጣትና ማን አለብኝነት፣ ደላላ-መር የገበያ ሥርዓት መንሰራፋት፣ የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ፣ ሕገወጥ ንግድ፣ የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት . . . ወዘተ ሁሉ በአንድ ተሰልፈው በምክንያትነት ቢቀርቡ አሁን ላይ እየተስተዋለ ላለው የዋጋ መናር መልስ ሊሆኑ ከቶም አይቻላቸውም። ይህ የአንድ ሰው ድምፅ ሳይሆን ወደ ገበያ የወጣ ሸማች ሁሉ የሚያጋጥመው ነው። እያንዳንዱ ዜጋ እየኖረው ያለ ኑሮ ሆኗል። እስኪ አንድ ሳሙና 60 ብር፣ አንድ ኪሎ ጤፍ መቶ ብር፣ የአንድ ኪሎ ቃሪያን ዋጋ 114 ብር መግባትን ምን ይሏል?

አሁን እንደምናየው መንግሥት ችግሩን ለመፍታት ግብረ ኃይላት ሲቋቋሙ ነው ። ሰሞኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይህንን አድርጌያለሁ እያለ ነው። ሃገራዊ የሆነውን የኑሮ ውድነት ችግር በዘላቂነት ለመከላከል ሸማቹም የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ሲያጋጥመው ግዥ ባለመፈጸምና ጥቆማ ከማድረግ ጀምሮ መረጃ በመስጠት ግብረ ኃይሉን በመደገፍ ለሙብቱ መቆም እንዳለበት ነው የሚገለጸው። ግን እስካሁን ምን ተገኘ? ከተባለ መልሱ "ምንም" ይመስላል። ለዚህ ደግሞ ከላይ እንዳልነው አይን ተጨፍኖ በተገለጠ ቁጥር ዋጋዎች ሰማየ ሰማያት ደርሰው መገኘታቸው ነው። ከሦስት ቀን በፊት በ79 ብር ይገኝ የነበረ አንድ (መቀመጫው ወገቡ ላይ የደረሰ) ብርጭቆ ጭማቂ በሦስተኛው ቀን በኋላ ሲሄዱ 100 ብር ሆኖ ሲያገኙት ምን ይላሉ? ወደ 4 ኪሎ ብቅ ካሉ ይሄ ሆነ "በቃ፣ ከዛሬ ጀምሮ ጁስ መጠጣት አቆምን ማለት ነው?" ያለችውን ወጣት አስተያየት ጨምሮ ያለውን) እውነት ያረጋግጣሉና ገበያው አብዷል በሚያስብል ደረጃ ላይ ደርሷል።

የብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ምክር ቤት ባወጣው መግለጫ፤ "አሁንም በኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ፈተና እየገጠመን ያለው ከዋጋ ግሽበት ጋር በተገናኘ ሲሆን፥ ከአምናው የሚያዚያ ወር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ግሽበቱ 36 ነጥብ 6 በመቶ ደርሷል። ነገሩን ይበልጥ ከባድ የሚያደርገው ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እየተመዘገበ ያለው የምግብ ነክ ሸቀጦች ላይ መሆኑ ነው፡፡" በማለት መግለፃቸው ይህንኑ እያልን ያልነውን ከማረጋገጥ በላይ የሚለው የለውም።

ይህንን የገበያ ሁኔታ ለማረጋገጥ በተለያዩ ስፍራዎች በመዘዋወርና ሸማቾችን በማነጋገር ሁኔታዎችን ለማረጋገጥ የተሞከረ ሲሆን፣ ቀዳሚ ያደረግነው ወደ አቅራቢያችን ወደሚገኘውና ከገበያው ጋር ያላሰለሰ ትስስር ወዳለው አንድ ክበብ ነው።

በጉዳዩ ላይ የክበቡ ሥራ ኃላፊ የሆነችውን፣ ወይዘሪት ሃና ኪዳኔን አግኝተን አነጋገርናት። በ"ያው እንደምታውቀው ነው" አይነት አሳሳቅ ነበር የተቀበለችን።

እንደ ሥራ ኃላፊዋ ሃና አገላለፅ፣ ምንም ነገር ባለበት ሁኔታ ለሳምንት አይቆይም። ሁሉም ነገር ከአቅም በላይ እየሆነ ነው። ፓስታ (በኪሎ) 65 ብር፣ ካሮት 60፣ ቀይ ስር 35፣ ጥቅል ጎመን 35፣ ድንች 30፣ ደረቅ እንጀራ 15 (ባለ 20ም አለ)፣ ያልተቀላ አተር 90፣ ባለ5 ሊትር ዘይት 900፣ ፉርኖ ዱቄት 80፣ ጥቁር ጤፍ 86፣ ነጭ (አንደኛው) 100 ብር . . . ነው እየተሸመተ ያለው። ይህ እስካነጋገርናት ቅዳሜ እለት ድረስ ያለ ገበያ ነው።

ወደ 6 ኪሎ - መነን አካባቢ አቅንተንም የሚመለከታቸውን ሰዎች ያነጋገረን ሲሆን፤ አንዷም የናሆም ምግብ ቤት ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ እቴነሽ ናቸው።

ወይዘሮ እቴነሽ እንደሚሉት ፤ገበያው ወይዘሪት ሃና ካለችው የተለየ አይደለም። እንደውም እንቁላል፣ ቅቤ . . . እና የመሳሰሉት ሲጨማመሩ ገበያው እናት ያዞራል ባይ ናቸው። "አብዶ አሳበደን። የምግብ ዋጋ ተመን ለማውጣት እንኳን እስኪያቅተን ድረስ ነው እያሻቀበ ያለው።" ሲሉም ነው ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ የሚገልፁት።

የገንዘቡስ ጉዳይ ብለናቸውም፣ "የቱ ብር፣ ምን ብር አለና፤ ዝም ብለን ተሸክመን እኮ ነው የምንዞረው፣ ምንም የሚገዛው ነገር የለም።" የሚለው ነበር መልሳቸው።

ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት ከነጋዴው በተሻለ ለሸማቹ ያቀርባሉ የተባሉትን፣ የእሁድ ገበያ ተራዎችንም ለመጎብኘት ሞክረናል።

ባደረግነው ሙከራ መሠረት የተመለከትነው (ሁሉም በኪሎ ነው) ቲማቲም 25፣ ፓፓያ 40፣ ሽንኩርት 30፣ ቀይ ስር 40፣ ድንች 28፣ ቃሪያ 114፣ ምስር 135 መሆኑን ሲሆን፣ ሌሎች ምርቶችም ከሌሎች መደብሮች ብዙም የተለዩ ሆነው አላገኘናቸውም።

ይህ ዘንድሮ ብቻ ሳይሆን ባለፈው ዓመትም ሸማቹን ኅብረተሰብ ለስቃይና ለሸመታ አቅም መዳከም የዳረገ የግብይት ሥርዓት ሲሆን፣ እንደ ማሳያም "ባለፈው ዓመት (ግንቦት 2014 ዓ.ም) በፍጆታ ምርቶች ላይ እየጨመረ የመጣውን የገበያ ዋጋና የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት መንግሥት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳ ከተማ ነዋሪዎች ጠየቁ።" በሚል በዜና እወጃ መልክ የቀረበውን የክልሎች ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል።

ይህም ሆነ ሌሎች ዜናዎች አየር ላይ ሲውሉ፣ መንግሥት የሕዝቡን ድምፅ ይሰማል፤ ችግሩም በዛው ይቀረፋል በሚል ብዙዎች ተስፋ ቢያደርጉም፣ ሁኔታው ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ እዚህ ደርሷል። እዚህ መድረስ ብቻም ሳይሆን፤«የኑሮ ውድነት ጉዳይ የእኛ ኃላፊነት አይደለም» የሚል አስተያየት ከወደ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተሠራ ዜና አማካኝነት ብቅ ብሏል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወ/ሮ በላይነሽ ረጋሳ ባለፈው ሐሙስ መጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም አዲስ ዘመን ለንባብ አብቅቶት በነበረው ዜና አጠቃላይ የኑሮ ውድነቱን በተመለከተ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደማይመለከተው፤ እንዲሁም፣ ዋጋ ባልወጣበት ነገር ላይ መሥሪያ ቤታቸው ኃላፊነት መውሰድ እንደማይችል ገልጸዋል። ይህ ያስኬዳል? ወደ ፊት የምናየው ይሆናል።

ይህንን የተፈጠረውን ከፍተኛ የዋጋ ንረት፣ ወይም የኑሮ ውድነት አስመልክተን የተለያዩ ምሑራንን ለማነጋገር ጥረት ያደረግን ሲሆን፣ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ፍቃደኛ የሆኑት በቅድስተ ማሪያም ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር፤ አቶ ኤርሚያስ ብርሀን የሚከተለውን አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

መምህር እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሥራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ከፍተኛ የጥናት ባለሙያ የሆኑት አቶ ኤርሚያስ እንደሚሉት፤ በአሁኑ ሰዓት ምንም አይነት ጥናትም ሆነ ምርምር በማያስፈልገው መልኩ ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት ይታያል።

ጉዳዩን ከኢኮኖሚክስ ሕግ አኳያ እንየው ከተባለ የዋጋ ንረት፣ ወይም የኑሮ ውድነት ባለ ድርሻ አካላቱ ብዙ ናቸው። የእነዚህ ባለ ድርሻ አካላት እንቅስቃሴና ተግባር በገበያው ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። አሁን ባለው ሁኔታ እየታየ ያለው ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እና የኑሮ ውድነት ስለሆነ ከእሱ አኳያ እንነጋገር የሚሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው "ምክንያቶች" የሚሏቸውንም እንደሚከተለው ገልጸዋቸዋል።

ለዋጋ ንረት ምክንያቶች በርካታ ሲሆን፣ ቀዳሚው የፍላጎትና ምርት አለመጣጣም፣ ማለትም ፍላጎት ከፍ ሲልና ምርት ሲያንስ እውነተኛ የዋጋ ጭማሪ ሊሆን ይችላል። የአንድ ሀገር ፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ሰላም ሁኔታ፣ ስጋት (በተለይ በሸማቹ በኩል ነገ የባሰ ሊወደድ ይችላል፣ ላይገኝም ይችላል ከሚል የሚመጣ ስጋት)፤ ግሽበት፤ሕገወጥ ክምችት መፍጠርና መደበቅ) በተለይ በአንዳንድ ሕገወጥ ነጋዴዎች በኩል ሊታይ የሚችል ሁኔታ ሲሆን፣ እሱም "ምርቱ ነገ ላይገባ ስለሚችል በውድ ልሸጠው እችላለሁ" ከሚል የሚመጣ የግለኝነት ስሜት፤ እጥረት ይኖራል ከሚል የሚመጣ ያልተገባ ሽሚያ፣ የሕግ መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ የሕግ ክፍተቶች መኖር ወዘተ ለእንደዚህ አይነቱ የግብይት ሥርዓት (ዋጋ ንረት) ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው።

መምህር፣ የኢኮኖሚ ባለሙያና ተመራማሪው አቶ ኤርሚያስን ስለ መፍትሔዎቹም አንስተንባቸው ነበር። እንደ ባለሙያው ከሆነ መፍትሔውም፣ ልክ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ፣ በርካታ ባለ ድርሻ አካላት አሉት።

የመጀመሪያውና ትልቁ ሚና የመንግሥት ሲሆን፣ እሱም ሀብት (ሪሶርስ)ን ማከፋፈል ላይ መሥራትን፣ ሰላምና የፖለቲካ መረጋጋትን መፍጠር፣ (እንደ ዘላቂ መፍትሔ) ምርት የሚጨምርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ መካከለኛና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ሴክተሮችን በማስፋት፣ የሕግና ቁጥጥር ሥርዓትን ማጥበቅና ከሕግ ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ማስተካከል እና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወንን ይመለከታል።

ከኅብረተሰብ የተደበቀ ምንም ነገር የለምና ከማንም በላይ ሸማቹ ሁሉንም ነገር በቅርብ ያውቃል። በሰፈር፣ በመደብር በአካባቢ፣ ... ያውቃል። ከነጋዴው ጋር አብሮ ነው የሚኖረው። በመሆኑም፣ ሕጋዊውን ሕጋዊ ካልሆነው በመለየት በኩል ሊጫወተው የሚችለው ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም፣ ላልተፈለገ የዋጋ ንረትና ጭማሪ ከመጋለጡ በፊት የግብይት ሥርዓቱ ሥርዓት እንዲኖረው የማድረግ ድርሻውን መወጣት ይገባዋል። ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው ከመንግሥት ጋር በመሆን ስለሆነ በዚሁ አግባብ መሥራትን ይጠይቃል ይላሉ አቶ ኤርሚያስ። ሸማቹም እንደ አንድ ባለ ድርሻ አካል ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት መሆኑንም ይናገራሉ። በዚህ ደግሞ ተጠቃሚው ማንም ሳይሆን ራሱ ሸማቹ ነው።ስለዚህ ለሕገወጥ ተግባር ተባባሪ ባለመሆን ኃላፊነቱን መወጣት አለበት።

አቶ ኤርሚያስ በነጋዴው ማኅበረሰብ በኩል ያለውንም አንስተዋል። እንደ እሳቸው ሙያዊ አስተያየት ጉዳዩ ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፎ በኃላፊነት አብሮ የመሄድ ጉዳይ ነው። ነጋዴው ለሸማቹ አስፈላጊው እንደሆነው ሁሉ፤ ሸማቹ ለነጋዴው አስፈላጊ ባለድርሻ አካል መሆኑን በሚገባ ማወቅ አለበት። በመሆኑም ደንበኛው የሚጎዳበትን መንገድ በፍፁም መፈለግ የለበትም። የሚያስፈልገውና ገበያውን ጤናማ የሚያደርገው የሁለቱ ተደጋግፎ መሄድ ነውና ነጋዴው ለዚህ መርሕ መገዛት ይገባዋል። ተገቢ ያልሆነ ትርፍን መሻት የለበትም፤ ሕገ ወጥ በሆነ ንግድ ላይ መሠማራት የለበትም፤ አላስፈላጊና ምስጢራዊ ክምችትን በመፍጠር የግብይት ሥርዓቱን በግል ጥቅም በመለወጥ አላስፈላጊ መጨናነቅንና ትርምስን በሀገር ላይ መፍጠር አይገባውም። ይህ ሄዶ ሄዶ ራሱን፣ የንግዱን ማኅበረሰብ ነው የሚጎዳው። በርካታ ነገሮችንም ያሳጣል። በመሆኑም፣ ከእንደዚህ አይነቶቹ ሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ራሱን በማፅዳት ለግብይት ሥርዓቱ ሥርዓታማነት የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት። በዚህ ደግሞ የመጀመሪያው ተጠቃሚ ራሱ ነጋዴው ነው።

ባለፈው ዓመት የነበረውን የዋጋ ንረት ሁኔታ በተመለከተ በርካታ ሥራዎች ተሠርተው የነበረ መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በጥቅምት እና ኅዳር 2014 ዓ.ም 4 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ እና 12.5 ሚሊየን ሊትር የምግብ ዘይት መግዛቱ፤ እርምጃውም የገበያ ዋጋን ለማረጋጋት ያለመ መሆኑን ሚኒስቴሩ ገልጿል።

የአዲስ አበባ መስተዳድር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን ለመርዳት በማሰብ የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ለሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን ለማቅረብና የእህል የገበያ ዋጋን ለማረጋጋት እስከ 500 ሚሊዮን ብር ብድር ሰጥቶ እንደነበር ይታወሳል።

ባለፈው ዓመት ነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኑሮ ውድነት ለመቅረፍ መሠረታዊ ሸቀጦችን በመደጎም ያቀደውን የዋጋ ግሽበት ከሁለት አኃዝ ወደ አንድ አኃዝ ለመቀነስ አቅዶ ሲንቀሳቀስ የነበረ መሆኑ፤

የዚሁ የኑሮ ውድነቱን ችግር ለመቅረፍ፣ በተለይ ሕገወጡን ክፍል ሥርዓት ለማስያዝ የተቋቋመው ግብረ ኃይል "ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ያለው ግብረ ኃይል ለኢንዱስትሪና ለግብርና ፍጆታ የሚውል ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሳይኖር የዋጋ ጭማሪ በማድረግ በኅብረተሰቡ ላይ ለከፋ ችግር በሚዳርጉ ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ እርምጃ ሲወስድ" የነበረ መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው። ጥያቄው፣ "ዘንድሮስ?" የሚል ነው።

በመጨረሻም፣ ገበያውን ሥርዓት በማስያዝ በኩል መንግሥት የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወስድ የሚያከራክር አይደለም። ለዚህ ማስረጃው ደግሞ ከላይ የጠቀስናቸውና የተከናወኑ ተግባራት ናቸው። አሁንም፣ ሰሞኑን አንድ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊ እንደሰጡት፣ ሕገወጥ ንግዱን የሚያበረታታና የ"አይመለከተንም" መግለጫ ሳይሆን መንግሥት እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ወገቡን አስሮ ሊሠራና የዜጎችን ኑሮ የተረጋጋ ሊያደርግ ይገባል። የኑሮ ውድነትን በማርገብ ረገድ ትልቁ ድርሻ የመንግሥት ነው። የሀገርን ሰላምና ፖለቲካዊ ሁኔታዎን ማስተካከል፤ አርተፊሻል የኑሮ ግሽበት እንዲፈጠር በሚያደርጉ አካላት ላይ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራት መሆኑን በመፍትሔነት አንስተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ችግር ያስተማራት ለሌሎች የተረፈች ነፍስ

**እፀገነት አክሊሉ**

የምሥራች ዓለሙ ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው ከአዲስ አበባ በ76 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ሞጆ ከተማ ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷንም በሞጆ ቁጥር አንድ ትምህርት ቤት ተከታትላለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ እዚያው ሞጆ ከተማ ላይ ቁጥር ሁለት በሚባለው ተምራለች። ከ12ኛ ክፍል በኋላ ያለውን ትምህርቷን ግን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ገብታ ለመቀጠል አልቻለችም። ለዚህ ደግሞ ምክንያት አላት። ለመኖርና ራሷን በሌላ መንገድ አብቅታ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ለመድረስ መፈለጓ አንዱ ነበር።

ለሕልሟ መሳካት ያግዛት ዘንድ 12ኛ ክፍል ፈተናዋን እንደተፈተነች የጸጉር ሥራ ሙያ ተማረች። በዚህ ትምህርቷም ያገኘችውን እውቀት ይዛ ወደ ተወለደችበት ከተማ አቀናች። ጸጉር ቤት ውስጥ በመቀጠርም ሥራዋን አሀዱ አለች። ተቀጥራ ትሠራባት የነበረችው የጸጉር ቤት ባለቤት መልካም እይታ ያላት ነበረችና የሥራ ብቃታቸውን በማየቷ እርሷን ጨምሮ ሁለት ሴቶችን አዲስ አበባ ሄደው የሚሠሩበትን እድል ሰጠቻቸው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ለየምሥራች ብዙ ነገሮቿን ያመቻቸላት ሆነ።

"... አዲስ አበባ በተሰጠኝ እድል ተጠቅሜ የተሳካ ጊዜ እንዳሳልፍ ሆኛለሁ። በሥራውም በኑሮም ጥሩ የሚባል ሁኔታ ውስጥም አስቀምጦኛል። ነገር ግን ሕይወት ሁልጊዜም ቢሆን አዲስ ነገርን ይፈልጋልና እኔም አዲስ አበባ ከተማ ላይ እየሠራሁ ያለሁት የጸጉር ቤት ሥራ ለጊዜው የሚያኖረኝ ቢሆንም ነገን የተሻለ ለማድረግ ግን አያስችለኝምና ሌሎች አማራጮችን ማየት እንዳለብኝ ተሰማኝ።" ትላለች የአዲስ አበባ እድሏንና የሥራ ጉዞዋን ስታነሳ።

የምሥራች ይህ የለውጥ ፍላጎቷ ከእለት እለት እየጨመረ በመምጣቱ ምን ባደርግ ነው በሕይወቴ ላይ ለውጥ የማመጣው ብላ ስታስብ ያገኘችው ምላሽ ወይም አማራጭ ወደ ዓረቡ ሀገር መሄድ ነበር። አደረገችውምና ኩዌት ሄደች። ሆኖም በብዙ ነገር ተፈትና ነበር። ሁኔታውን ስታስረዳ እንዲህ ነበር ያለችው "... ሕይወት ለውጥ ያስፈልጋታል ብዬ በማሰብ ነበር የሄድኩት። እንደ አብዛኞቹ እህቶቼ በቤት ሠራተኝነት ለመሥራት። ሆኖም እዛም ከደረስኩ በኋላ ብዙ ነገሮች ፈተና ሆኑብኝ። ከቋንቋ ችግር ጀምሮ በቀላሉ ነገሮችን ለመልመድ ከባድ ነው። የባዕድነት ስሜቱም ከፍ ያለ ነበር።"

እነዚህ ፈተናዎች ከምታስበው በላይ ቢሆኑባትም ጉዞዋ ዓላማ ያለው ነበርና ራሷን ከሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ዓመታትን ቆይታለች። ከሰዎቹ ባሕሪና ከሀገሩ ባሕልና ወግ ጋር ለመግባባት ጥረት አድርጋለች። ይህም ሆኖ ግን መጀመሪያ ከገባችበት ቤት ብዙም ሳትቆይ ነበር የወጣችው። እንደ አብዛኞቹ አሠሪዎች መጀመሪያ የገባችበት ሴት አልተመቻትም። የገባችበት ቤት ባለ አራት ወለል ፎቅ የነበረ ሲሆን፤ አምስት ወንድ ልጆች በቤቱ ውስጥ ይኖራሉ።

የምሥራች ሥራዋ ደግሞ አራቱን ወለል ሕንጻ ማጽዳትና የልጆቹን መኝታ ክፍል ማዘጋጀት ነበር። በዚህም በቀላሉ ለመግባባት ተቸገረች። እናም ከወር በላይ እዚያ ቤት ውስጥ መቆየት አልቻለችም። በአግባቡና በትሕትና ያመጣት አገናኝ (ኤጀንሲ) ጋር እንድታደርሳት አሠሪዋን ለመነቻት። ሴትየዋም በሁኔታው በመናደዷ የቆየችበትን ደመወዝ ከልክላ አገናኙ ጋር አደረሰቻት። የምሥራችም ደመወዟን መከልከሏ ምንም ሳይመስላት ከቤቱ ወጥታ አገናኞቹ ጋር መድረሷ ለእሷ ትልቅ ድል ሆነላት።

ኤጀንሲው ሌላ ሁለተኛ ቤት ፈልጎ አስገባት። ይህኛው ቤት ደግሞ የተለየ ነው። የተፈናቃዮች መንደር አካባቢ የነበረና ራሳቸውን እንኳን በቅጡ ማስተዳደር ያልቻሉ ሰዎች ቤት ነበር።የምሥራች እዚህ ደግሞ ሌላ ፈተና ገጠማት። ሰዎቹ ተፈናቃዮች ከመሆናቸው የተነሳ ገቢያቸውም ያን ያህል አመርቂ አይደለም። እሷ ደግሞ ሠርታ ለማግኘት ከአገሯ የወጣች ናት፤ በዚህ መካከል እነዚህ ሰዎች ደመወዝ ይከፍሉኛል አይከፍሉኝም የሚለው ያሳስባት ጀመር። ይህም ቢሆን ግን ሁሉንም ተቋቁማ ለመሥራት ብትፈልግም ሁኔታው ግን ከአቅሟ በላይ ሆነ። በመጨረሻም ሴትየዋ ያመጣቻት ቦታ የ21 ቀን ደመወዟን ሰጥታ አደረሰቻት። እድል ከእሷ ጋር የሆነችላት የምሥራች እወጣለሁ ባለችባቸው ቤቶች ሁሉ ሰዎች ሳይጣሏት በትሕትና ያመጧት ቦታ መልሰው ያደርሷታል። አሁን ሦስተኛ ቤቷ ላይ ደርሳለች። በልቧ ፈጣሪዋን እየለመነች ወደቤቱ ለሥራ ገባች። ሦስተኛው ቤቷ የተሻለ ሰው ያገኘችበት ነው። ባለቤቷ ሁለት ልጆች አሏት። ከእርሷ በፊት የገባች የፊሊፒንስ ዜጋም አለች፤ ሹፌርም አለ፤ ቤቱም ፎቅ የሌለው ቪላ ቤት ነበር። በዚህም ጥሩና ደስተኛ ሆና መሥራቷን ቀጠለች። የእርሷ የሥራ ድርሻ የምግብ ሥራ ነው። በዚህም ሦስት ያህል ዓመታትን በቤቱ ውስጥ አሳልፋለች። በመካከል ሁለት ዓመት ሲሞላት ለእረፍት ሀገሯ ቤተሰቦቿ ዘንድ ደርሳ ነበር የተመለሰችው።



የምሥራች ዓለሙ፤

የምሥራች ሁሌም ለውጥ ናፋቂ ናትና ሀገሯ ደርሳ ስትመለስ አንድ ሃሳብ መጣላት ፤ እሱም ከሰው ቤት ወጥታ ራሷን ችላ መሥራትና ራሷን በበለጠ ሁኔታ መቀየር የሚል ነበር። ይህንን ሃሳቧንም ለአሠሪዋ እንደሄደች ነገረቻት፤ ሴትየዋም የተባረከች ነበረችና ፍላጎቷን አክብራ ነገር ግን ለእሷ የሚሆን ታማኝና ጎበዝ ሰው እንድታመጣላት ነገረቻት። የምሥራችም በሀሳቧ በመስማማት ከኢትዮጵያ የምትተማመንበትን ሰው በማምጣት ሁለት ወር አለማምዳላት ወጣች። ይህም የአሠሪና የሠራተኛ ግንኙነታቸውን ከፍ ወዳለ ወዳጅነት አሸጋገረው። እንደ ቤተሰብ የሚተሳሰቡ የሚጠያየቁ በችግር በደስታ የሚገናኙ አደረጋቸውም።

አሁን የምሥራች ሌላ ዓለምና ኑሮ ለመመሥረት አሰበች፤ ከዚህ ቀደም እረፍት ስትወጣ የተዋወቀቻቸው ኢትዮጵያውያን እህቶቿ ደግሞ ሥራ እስከምታገኝ ማረፊያዎቿ ሆኑላት። ከዚያም ሥራ ማፈላለግ ጀመረች። እሷ እንኳን ሀገር ቤት በተማረችው የጸጉር ሥራ ለመቀጠር ነበር የፈለገችው። ቢሆንም ጓደኞቿ ግን ሥራው ረጅም ሰዓትን የሚወስድ በመሆኑ እንደ እኛ ሱቆች ላይ ሥሪ ብለው አማከሯት። እሷም በሃሳባቸው ተስማምታ ደመወዙ ዝቅ ያለ ቢሆንም ሱቅ ተቀጥራ እቃ መሸጡን ተያያዘችው። ይህንን እየሠራችም በመኖሪያ ፍቃዱ የሚያኖራት (ስፖንሰር የሚያደርጋት) ማፈላለግ ያዘች። በዚህም ተሳክቶላት በማግኘቷ የሥራ ፈቃዷን በአገኘችው ስፖንሰር በማዞር ሥራዋን በከፍተኛ ሞራል መሥራቷን ቀጠለች።

የምሥራች ሱቅ ቆሞ ከመነገድ ወደ ትልልቅ ካምፓኒዎች የጅምላ ንግድ ማሻሻጥ (ሴልስ) ውስጥ ገባች። ኮሚሽን እያገኘች በማሻሻጥም ጥሩ ገቢን ማግኘት ጀመረች። ነገር ግን ይህንን የሞቀ ሥራዋን የሚያቀዘቅዝ ነገር ተፈጠረ። እሱም ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ነበር። ኮቪድ ባመጣው ችግር ምክንያት ሱቆች ተዘጉ። እንደ ቀድሞው አሻሻጮች (ሴልሶች) የሚያስፈልጉት ነገር ጠፋ። ከዚያ ይልቅ ሰዎች በበይነ መረብ (በኢንተርኔት) ቀጥታ ግብይትን ጀመሩ። ይህ ደግሞ ካምፓኒዎቹ የሠራተኞቻቸውን ቁጥር እንዲቀንሱ አስገደዳቸው፤ ከተቀናሾቹ መካከል ደግሞ የምሥራች አንዷ ሆነች።

ይህ ጊዜ ለየምሥራች አቅጣጫዋን ወደሌላ መንገድ መቀየሪያ ነበር። ማወቅ መቼና እንዴት እንደሚጠቅም አይታወቅምና የምሥራችም ሀገሯ ላይ ተምራው የሄደችው የጸጉር ሥራ ሙያ አሁን ላይ አስፈለጋት፤ ምናልባት ከዘመኑ ጋር ማጣጣም ይገባት ይሆናል እንጂ መሠረታዊው እውቀት ያላት በመሆኑ አልተቸገረችም። በዚህም ትንሽ ዘመናዊ የሆኑ የጸጉር ቤት እቃዎችን አጠቃቀም ማወቅ እንዲሁም አንዳንድ ወቅታዊ የፋሽን ነገሮችን መረዳትን ተማረችና በአነስተኛ ደመወዝ አንድ ጸጉር ቤት ተቀጥራ ጊዜውን ለማለፍ ተጠቀመችበት። ራሷን ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም በቤቱ ውስጥ አንዳንድ እቃዎችን ገዝታም በመለማመድ ሥራውን ተቀላቀለች።

"...እኔ ውጪ ስወጣ ምን እንደሚገጥመኝ አላውቅም ነበር፤ ነገር ግን እድለኛ ሆኜ ፈጣሪም አግዞኝ የከፋ ነገር አልገጠመኝም። ስኬታማ ሆኛለሁ ፤ ነገር ግን በርካታ እህቶቼ ስለው የሚመጡት ነገርና ነባራዊው ሁኔታ አልጣጣም ብሏቸው ብዙ ችግር ውስጥ ገብተዋል፤ እየገቡ ያሉም አሉ። ለእነሱ ደግሞ ድምፅ ልሆናቸው በምችለው ሁሉ ሌሎችን አስተባብሬ ላግዛቸው ብዙ እንቅስቃሴዎችን እያደረኩ ነው" የምትለው የምሥራች፤ ዛሬ ላይ በኩዌት ትልቅ የሚባል ጸጉር ቤት ውስጥ ተፈላጊ ሆና ትሠራለች። የዛሬ ሰባትና ስምንት ዓመት ስለእኛ በዓረቡ ዓለም በተለይም በኩዌት ስለሚኖር ዜጎች ግድ የሚለው ምንም ዓይነት ኮሚኒቲ አልነበረንም የምትለው የምሥራች፤ በጊዜው አንድ ሰው ተቸገረ ሲባል እንዲሁ በበጎ ፈቃድ የአቅማችንን ማድረግ ነበር። ይህ ግን ማንም ምንም የሚጠቅም ስላልነበር ሌሎች ነገሮችን ማሰብ ጀመርን በማለት ትናገራለች።

ኢትዮጵያውያን በሰው ቤት ሲሠሩ፣ ሳንባቸው ሲታመም። የካንሰር ተጋላጭ ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜም ከጫና መብዛት የተነሳ ለአዕምሮ ሕመም ሲጋለጡ አሠሪዎቻቸው ከነደንብ ልብሳቸው አስወጥተው ይጥሏቸዋል። በጣም የተሻሉ ካሉ ደግሞ ሐኪም ቤት አድርሶ የመሄድ ሁኔታዎች ያጋጥማሉ። እናም የምሥራችና ጓደኞቿ ይህንን ችግር ለመቅረፍ «በኩዌት የኢትዮጵያውያን ወጣቶች ማኅበር» በሚል ማኅበር መሠረቱ።

በማኅበራቸው አማካይነትም በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ የገቡ እህቶችን ቫዝሊን። የሴቶች ንጽሕና መጠበቂያዎች። የጥርስ ሳሙናና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን አዋጥቶ በመግዛት በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ እየሄዱ መጠየቅ ጀመሩ። ከሁሉም በላይ ደግሞ በኩየት የኢትዮጵያ ኤምባሲ የሚያሳየው ምንም አይነት ተሳትፎም ሆነ ሥራ ያልነበረ በመሆኑ ኤምባሲው ስለ ዜጎቹ ደህንነት እንዲያስብ የማድረግና የማነቃቃት ሥራንም እንዲሠሩ ሆኑ። ይህ ሥራቸው ደግሞ ብዙ ሰዎችን ተስፋ የሰጠ ወደ ጤናቸውና ሀገራቸው የመለሰ ነበር።

"...በወጣት ማኅበሩ ብዙ ነገሮችን ስንሠራ ቆይተናል። አስር ቤት ያሉ እህት ወንድሞቻችንን እንጠይቃለን። ጉዳያቸውን እንፈጽማለን፤ የታመሙትን እናሳክማለን፤ እንጠይቃለን፤ በሕይወት ሲያልፉም አስከሬናቸው በክብር ወደሀገራቸው እንዲሸኝ እናደርጋለን። ኋላ ላይ ግን ይህ ማኅበር ለምን ወደ ኮሚኒቲ ደረጃ አድጎ ሕጋዊ እውቅናን አያገኝም በማለት ምርጫ ተደርጎ የመተዳደሪያ ሕገ ደንብ ጸድቆ በሥነ ሥርዓት ወደ ሥራ ገብተናል" ትላለች። ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ጀምሮ እውቅና ባገኘው ኮሚኒቲ ውስጥም የምሥራች መሥራች አባል በመሆን በርካታ ሥራዎች እንዲሠሩ ማድረጓን ትገልጻለች።

በዋናነት ኤምባሲው ሕጋዊ መንገድን እንዲከተሉ የሚያደርጉ ደብዳቤዎችን እንዲሰጣቸው ማስቻል ላይ ብዙ ለፍታለች። በተለይም ማረሚያ ቤቶች አካባቢ ሲሄዱ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጽፉላቸው ማድረጉ ላይ ከኤምባሲው ጋር የተጠናከረ ሥራ ከሠሩት መካከል ነች። «ስለዜጋችን ግድ ይለናል» በሚል በበጎ ፍቃድ የሚሠሩት ይህ የኮሚኒቲ ሥራቸው ኢትዮጵያውያን ተረጋግተው ሥራቸውን እንዲሠሩ አድርጓቸዋል። በደል ሲኖርባቸው እንዲያወጡት፤ መፈታት የሚችለው እንዲፈታ የማይሆን ከሆነ ደግሞ በአካላቸው እንዲሁም በጤናቸው ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስ በሰላም ሀገራቸው እንዲገቡ በማድረግ በኩልም ብዙ መፍትሔ የቸራቸው ሆኗል።

አሁን ላይ 20ሺህ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን በኩዌት ሀገር በተለያዩ የሥራ መስኮች ላይ ተሠማርተው የሚገኙ ሲሆን፤ እነዚህ ዜጎች ደግሞ ትዳር መሥርተው ፤ ልጆች ወልደው ያስተምራሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ፈተናዎች ይኖራሉ። እናም ይህንን ለመፍታትም ኮሚኒቲው መዋዕለ ሕጻናትን በመክፈት ተጠቃሚ የማድረግ አቅድ ይዟል። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች አገሮች እንደሚያደርጉት የሀገራችንን ምርት እዚያ ወስደን ለዜጋውም ለሌላውም ለመሸጥ አንደ ሱፐር ማርኬት አይነት የገበያ ማዕከላትን የመክፈት አቅድ ተይዟል ትላለች የምሥራች።

"...አንድ ለቤት ሠራተኝነት ከአገሯ የምትወጣ ሴት በምን መልኩና ምን ዓይነት ዝግጅት አድርጋ መሄድ እንዳለባት መንግሥትና ኤምባሲዎች እየሠሩ ያለው ሥራ አለ፤ ነገር ግን ይህም ቢሆን ሕገወጥ ደላሎች አሁንም ድረስ ምንም የማያውቁ የገጠር ልጆችን ነው የሚልኩት ፤ ቋንቋ መሞከር እንኳን አይችሉም። ያንን ከባድ የሆነ የዓረቦች ባሕሪም መቋቋም አይችሉም፤ በመሆኑም ምንም ሳያውቁ የሚመጡት እህቶቻችን ከፍ ላለ ችግር እየተጋለጡ ነው" የምትለው የምሥራች፤ በአሜሪካና አውሮፓ ሕግ የበላይ ነው። ማንኛውም ሰው መብቱና ደህንነቱ ይጠበቃል። ዓረብ አገር ላይ ግን ሕጉ ሳይሆን ሰዎቹ ናቸው የበላይ። ይህንን የበላይነታቸውን ለማሳየት ደግሞ የተለያዩ ነገሮችን ይጠቀማሉ። አንድ ነገር እንኳን ሲሆን «እኔ እኮ ሀገሬ ነው» በማለት ራሳቸውን ከፍ ያደርጋሉ። በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር ትልቅ ትዕግስት ይጠይቃል። ነገር ግን ከአቅም በላይ ከሆነ ወደ ኤጀንሲ አልያም ኮሚኒቲው ጋር መሄድን መልመድ ያስፈልጋል ስትል ከተሞክሮዋ በመነሳት ትመክራለች።

አሁን በኤምባሲዎች በኩል ብዙ ለውጦች መኖራቸውን የምትጠቁመው የምሥራች፤ ዜጎች ምንም ዓይነት ጉዳት በራሳቸውም በሌሎችም ላይ ከማድረሳቸው በፊት ውሳኔያቸውን ማሳለፍ ይገባቸዋል። ሁሉም ሴቶች ለሥራ ሀገራቸውን ጥለው ከወጡ በኋላ ሊላበሱ የሚገባቸው ነገር ትዕግስት፤ ሆደ ሰፊነት፣ መቻል ከመጠን በላይ ከሆነ ደግሞ ወጥተው ሌላ ቤት የሚቀይሩበትን መንገድ መፈለግ እንጂ ወዳልተገባ ነገር ውስጥ ገብተው የራሳቸውንም የሌላውንም ተስፋ ሊያጨልሙ አይገባቸውም ትላለችም።

በኩዌት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ከደመወዝ ጋር በተያያዘ የነበሩ ልዩነቶችን በማጥበብ፤ ሌሎች በዜጎች ላይ ይደርሱ የነበሩ ጉዳቶችን በመቀነስ፤ በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት እንደ ዜጋ ለሀገራችን ምን እናድርግ በማለት ብዙ ሠርተናል። ለአብነትም ለመከላከያ ሠራዊት ድጋፍ የሚሆን አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ብር አስገብተናል። ከዚያም በጦርነቱ ምክንያት ለተጎዱና ለተፈናቀሉ ወገኖች አምስት ቤቶችን ለመሥራት ቃል ገብተናል። አሁን ላይ ሦስቱ አልቀዋል፤ ሁለቱም በመሠራት ላይ ናቸው። በሌላ በኩልም ወልዲያ ላይ ለተፈናቀሉ ዜጎች አልባሳትን የመለገስ ሠራ ተሠርቷል ብላናለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

በዛሬው ‹አዲስ ዘመን ድሮ› ዓምዳችን በ1965 በታኅሣሥ ወራት ለንባብ የበቁ ዘገባዎችን መርጠናል። ከመረጥናቸው ዘገባዎች አብዛኞቹ ወንጀል ነክ ናቸው። ግርምትም የሚያጭሩና ጥያቄን የሚፈጥሩ አሳዛኝ ክስተቶች በወቅቱ ተዘግበዋል፡፡

### እኅትማማቾች በካቲካላ ሞቱ

ወይዘሪት ብዙነሽ ገብሬና ወይዘሪት እመቤት ገብሬ የተባሉ እኅትማማቾች ፤የእህል አረቄ ጠጥተው ለሞት ያበቃቸው ወላጅ እናታቸው አረቄውን ካወጡ በኋላ አልጋ ሥር አስቀምጠውት ወደ ገበያ ሲሄዱ ከተቀመጠበት ቦታ አንስተው በመጠጣታቸው ነው። ሟቾቹ አረቄውን እንደጠጡ በያሉበት ተዘርረው ወድቀው ነበር፡፡ በኋላ ግን ሰው ደርሶ ለሕክምና ፍቼ ጤና ጣቢያ ተወስደው ሕክምና ቢደረግላቸውም ለመዳን ተስፋ በማጣታቸው በ፲ ሰዓት ልዩነት ሁለቱም ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡

በሁለቱ እኅትማማቾች ላይ ይህ የሞት አደጋ የደረሰው፤ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም በሰላሌ አውራጃ በግራር ጃርሶ ወረዳ በፍቼ ከተማ ውስጥ ነው። ወይዘሪት ብዙነሽ ገብሬ ዕድሜዋ ፳ ሲሆን ወይዘሪት እመቤት ደግሞ ፲ ዓመት መሆኑን የማስታወቂያ ክፍሉ ባገኘው ሪፖርት መሠረት አስረድቷል፡፡

**(ታኅሣሥ 21 ቀን 1965 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ቤት ሰርሳሪ የገደሉት ተቀጡ

ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ሲሆን ቤታቸውን በመጋዝ ቆርጠና በፋስ መጥረቢያ ሰርስሮ ሲገባ ነቅተውበት በዱላ ደብድበው የገደሉት ሰዎች በወንጀለኝነት ተከሰው እሥራት ተፈረደባቸው፡፡

አቶ ታደሰ መንግሥቱና አቶ ሁንዴ ፈይሳ የተባሉት የገደሉት ተመቾ ቅጣው የተባለው፤በፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል የሌብነት ሪኮርድ ያለው መሆኑ ታውቋል።

ተከሳሾቹ ሌባውን የገደሉት አቶ ቸርነት አርጋው የተባሉትን ሰው ቤት ሰርስሮ ሲገባ ቢነቁበት ባለቤቱን በመጋዝ ሊቆርጣቸው በመሞከሩም መሆኑ ተገልጧል። ሟቹ የሌብነት ወንጀል ሲፈጽም የተያዘው አዲስ አበባ ቀበና ቀበሌ ከአፈ ንጉሥ አረጋ ቤት አጠገብ መሆኑን አዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመስክሯል። ተከሳሾቹ ሌባው ቤት ሰርስሮ ሊገባ ሲል ነቅተው ይዘውት በመተባበር በዱላ መደብደባቸው አምነዋል። በሰው ምስክርም ተረጋግጦ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፩ኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው እያንዳንዳቸው በ፪ ዓመት እሥራት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው፡፡

**(ታኅሣሥ 18 ቀን 1965 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ባስ መኪና አስገድደው ቀሙ የተባሉት ፍርድ ቤት ቀረቡ

በሌሊት ከመሐል አውራ ጐዳና ላይ እየቆሙ በማስገደድ ባለተሽከርካሪዎችን ቀምተዋል በመባል የተከሰሱት አቶ ዳኘ ደቻሳ፤ አበበ ነጋሽ፤ ጥላሁን እሸቴና ተስፋዬ ገብሬ ወህኒ ቤት ገቡ፡፡

አራቱም ተከሳሾች መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ-ም ከምሽቱ ፩ ሰዓት ተኩል ሲሆን አዲስ አበባ ፲ኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ አቶ ዓለማየሁ ዳምጤ የተባሉት ሰው መኪናቸውን በማስገደድ አስቁመው 79110 የሆነ ሽጉጥ መንጠቃቸውን የቀረበባቸው የዓቃቤ ሕግ ክስ ይገልጣል።

እነ ዳኘ ሰላማዊውን ሰው መኪናቸውን ከአስቆሙ በኋላ አባሪ ሆነው ከመኪናው ውስጥ በማንገላታት አስወጥተው ሽጉጣቸውን ከ፫ ጥይት ጋር ቀምተው ወስደው በፖሊስ መከታተል መያዛቸውን የአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፪ኛ ወንጀል ችሎት ተመስክሮባቸዋል፡፡

አራቱ ተከሳሾች ፍርድ ቤት ቀርበው በሰጡት ቃል ጥፋተኞች አለመሆናቸውንና ወንጀሉንም አለመፈጸማቸውን አመልክተዋል፡፡ የችሎቱ ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አመሠራረት የሚያስረዱ ምስክሮች መኖራቸውን ገልጠው ምስክር መስማት ተጀምሯል።

**(ታኅሣሥ 4 ቀን 19 65 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### በጥዳ ምክንያት የ9 ልጆች እናት ወህኒ ቤት ገቡ

በአንዲት የሞተች ጥጃ ምክንያት በተነሣው የወንጀል ክርክር አንዲት የ፵ ዓመት ሴት ፤ዘጠኝ ልጆቻቸውን ጥለው ወህኒ ቤት መግባቸውን ከአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተገኘው ዜና ታውቋል፡፡

እመት እልፍነሽ ወልደየስ የተባሉት የልጆች እናት ወህኒ ቤት ለመግባት ዋና ምክንያት የሆነባቸው አንዲት ጥጃ ገዝተው አርደዋል ተብለው ተከሰው ፍርድ ቤት ከቀረቡ በኋላ ነው፡፡

በተከሳሿ ላይ የቀረበው የዓቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያመለክተው ፤ጥጃዋ ከታረደች በኋላ ተደርሶበት የቀረቡት ምስክሮች ቆዳዋ የተገኘው ጥጃ እመት ጌጤ የተባሉትን ሴት ጥጃ ትመስላለች በማለት ምስክሮች ባሰሙት ቃል ብቻ መሆኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፫ኛ ወንጀል ችሎት የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ይገልጣል፡፡

እመት እልፍነሽ ፤በሞተች ጥጃ ምክንያት ተከሰው አዲስ አበባ አውራጃ ፍርድ ቤት ቀርበው በ፫ ወር እሥራት እንዲቀጡ ተፈርዶባቸው ወህኒ ቤት መግባታቸውን የተከሳሿ ጠበቃ ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ ገልጠዋል፡፡

**(ታኅሣሥ 18 ቀን 1965 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ

## ዋይት ሐውስ ኢራን እና አሜሪካ የእስረኞች ልውውጥ ሊያደርጉ ነው መባሉን አስተባበለ

ኢራን በሁለቱ አገራት መካከል የእስረኞች ልውውጥ ሊደረገው ማለቷ “ጭካኔ የተሞላበት” ሐሰተኛ መረጃ ነው ስትል አሜሪካ አስተባበለች። የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሁሴን አሚር አብዱላሂ እሁድ ዕለት ለመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በሰጡት አስተያየት፣ አገራቸው ከአሜሪካ ጋር እስረኛ ለመለዋወጥ መስማማቷን እና በቅርቡ ተፈጻሚ ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል።

ሆኖም የዋይት ሐውስ የደኅንነት ቃል አቀባይ ንግግሩን አስተባብለው የኢራን ባለሥልጣናትን ኮንነው፣ የሚኒስትሩ ንግግር የእስረኞችን ቤተሰብ ልብ የሚሰብር ነው ብለዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በኢራን ብሔራዊ ቴሌቪዢን ጣቢያ ቀርበው በአገራቸው እና በአሜሪካ መካከል ስምምነት መደረሱን በመጥቀስ “በአሜሪካ በኩል ነገሮች በጥሩ መልኩ ከቀጠሉ የእስረኞች ልውውጥ ሲደረግ በቅርቡ እናያለን” ብለዋል።

ጨምረውም አሜሪካ “ከፋይናንስ ጋር በተያያዘ ያሉ ጉዳዮችን ለመፍታት ስትሞክር” ኢራንም ዝግጁ ናት ብለው ነበር። ይህንን ንግግር ሐሰት ነው ያለው ዋይት ሐውስ በበኩሉ፣ ኢራን ውስጥ የታሰሩ ሦስት ዜጎቿን ለማስፈታት አሜሪካ ቁርጠኛ ናት ነው ያሉት ።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2016 የነዳጅ ኩባንያ ኃላፊ የሆነው የአሜሪካ እና የኢራን ጥምር ዜግነት ያለው ሲያማክ ናማዚ ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በመተባበር ኢራንን ሰልሏል በሚል ተከሶ 10 ዓመታት ተፈርዶበታል።

ሲያማክ ባለፈው ሳምንት በቴህራን እስር ቤት ውስጥ ለሲኤንኤን በሰጠው ቃለ መጠይቅ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን “ከዚህ ስቃይ እንድወጣ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያድርጉ” ሲል ጠይቋል። ኤማድ ሻርጊ የተባለው ሌላ የኢራን እና የአሜሪካ ዜግነት ያለው ባለሀብት እንደ አውሮፓውያኑ በ2018 በቴክኖሎጂ ላይ የሚሠራ ኩባንያ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ወደ አገሪቱ በተጓዘበት ጊዜ ታስሯል።

ሞራድ ታሃህባዝ የተባለው ሌላኛው የኢራን-አሜሪካ ዜግነት ያለው እና የብሪታኒያን ዜግነት ደርቦ የያዘ ግለሰብ፣ የኢራንን ሕግ ችላ በማለት እንዲሁም ለአሜሪካ መሰለል የሚሉ ክሶች ቀርበውበት እንደ አውሮፓውያኑ በ2019 የ10 ዓመት



ፍርድ ተበይኖበታል።ነገር ግን ባለፈው ሐምሌ ወር የኤሌክትሪኒክስ ቁጥጥር እየተደረገበት በዋስ የተለቀቀ ሲሆን፣ የዩናይትድ ኪንግደም ባለስልጣናት ሙሉ በሙሉ እንዲለቀቅ ከአሜሪካ ባለሥልጣናት ጋር በጋራ እየሠሩ መሆናቸውን መግለጻቸውን የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።



## ግዙፉ የሳዑዲ መንግሥት የነዳጅ ኩባንያ በታሪክ ትልቁን ትርፍ አስመዘገበ

ግዙፉ የሳዑዲ የነዳጅ ኩባንያ አራምኮ እኤአ 2022 161 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ማትረፉን አስታወቀ። ለኩባንያው ትርፍ መመንደግ የነዳጃ ዋጋ ማሻቀብና ብዛት ያለው ምርት ማቅረቡ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው። ኩባንያው በ2022 ያገኘው ትርፍ ከቀደመው ዓመት ትርፉ ጋር ሲነጻጸር የ46 ነጥብ 5 በመቶ ጭማሪ አስመዝግቧል።

አራምኮ ባለፈው ዓመት ሩሲያ ዩክሬንን ከወረረችና የነዳጅ ዋጋ ጣሪያ ከነካ በኋላ ትርፉን ይፋ ያደረገ ሌላኛው ኩባንያ ሆኗል። በተመሳሳይ ዓመት የአሜሪካው ሞቢል 55 ነጥብ7 በሊዮን ዶላር ያተረፈ ሲሆን የብሪታኒያ የነዳጅ ኩባንያ ሼል ደግሞ 39 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር አግኝቷል። አራምኮ ባለፈው ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ካገኘው ገቢ 19 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ለትርፍ ክፍፍል በዚህ ዓመት እንደሚያቀርብ አሳውቋል።

ክፍፍሉም አብላጫው የሚሄደው የኩባንያው 95 በመቶው ባለቤት ወደሆነው የሳዑዲ መንግሥት ነው። አራምኮ ከትናንት ወዲያ ባወጣው መግለጫ ያገኘው ከፍተኛ ትርፍ በድፍድፍ ነዳጅ ዋጋ መጨመር፣ ለሽያጭ ያቀረበው ምርት ብዛት እና በተጣራ ምርት ላይ ባሳየው መሻሻል የተደገፈ ነው ብሏል።

የአራምኮ ፕሬዚዳንት እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አሚን ናስር ኩባንያው ወደፊት ከነዳጅ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቅረፍ የነዳጅ እና የኬሚካል ምርቶቹን ከማስፋፋት በተጨማሪ ዝቅተኛ የካርቦን ልቀት ያላቸው ቴክኖሎጂዎች ላይ መዋዕለ ንዋዩን እንደሚያፈስ አስታውቋል።

በዓለም ከአሜሪካው አፕል በመቀጠል ሁለተኛው ከፍተኛ ሃብት ያለው ተቋም የሆነው አራምኮ፤ በአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ኩባንያዎች መካከል ተጠቃሽ ነው። አራምኮ ትርፉን ማሳወቁን ተከትሎ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ዋና ጸሐፊ አንገስ ካላማርድ በሰጡት አስተያየት ለአየር ብክለት ቁጥር አንድ መንስኤ የሆነውን ነዳጅ ሽጦ በአንድ ዓመት ውስጥ ከ161 ቢሊዮን ዶላር በላይ ማትረፍ አስደንጋጭ ነው ብለዋል።

ኃላፊዋ ጨምረውም ይህ ትርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኑሮ ውድነት በጨመረበት የሩሲያ ዩክሬን ጦርነትን ተከትሎ የጋዝ ዋጋ ከፍ ባለበት ጊዜ መሆኑ ይበልጥ አስደንጋጭ ያደርገዋል ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት





## ኢትዮጵያውን አትሌቶች በተለያዩ የጎዳና ላይ ውድድሮች ድል ቀንቷቸዋል

**ዓለማየሁ ግዛው**

እንዳለፉት በርካታ ሳምንታት ሁሉ ያለፈው እሁድ በተለያዩ የዓለም ከተሞች በርካታ የጎዳና ላይ ውድድሮች የተካሄዱ ሲሆን ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በትልልቅ ውድድሮች ድል አድርገዋል። ከነዚህ ውድድሮች መካከል አንዱ በሆነውና ከዓለም ታላላቅ የጎዳና ላይ ውድድሮች የሚጠቀሰው የ2023 የስፔን የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ሩጫ ነው። በዚህ ውድድር ወጣቱ ኦሊምፒያን አትሌት በሪሁ አረጋዊ ድልን ተቀዳጅቷል። ከሦስት ሳምንት በፊት በአውስትራሊያ ባትረስ በተካሄደው የዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ካሸነፈ በኋላ ፊቱን ወደ ጎዳና ላይ ውድድር ያዞረው አትሌት በሪሁ በስፔን ቪላ ዲ ላሬዶ ከትላንት በስቲያ በተካሄደው የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ የዓለማችንን ሁለተኛ ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ ነው ማሸነፍ የቻለው። አትሌቱ ውድድሩን በፍጹም የበላይነትና ተፎካካሪዎቹን በሰፊ ርቀት መርቶ ሊያሸንፍ ችሏል። ተጠባቂ በነበረው ፉክክር አትሌት በሪሁ ተፎካካሪዎቹን በሁለት ደቂቃዎች ልዩነት በመቅደም 26፡33 በሆነ ሰዓት ቀዳሚ ሆኖ ማጠናቀቅ ችሏል። የርቀቱ ዓለም ፈጣን ሰዓት ተመዝግቦ የሚገኘው ሪሆኔክስ ኪፕሩቶስ በተባለ አትሌት ሲሆን የተመዘገበውም ከሦስት ዓመታት በፊት በስፔን ቫሌንስያ በተደረገ ውድድር ነበር። በወቅቱም የተመዘገበው 26፡24 ሰዓት ነው። የ22 ዓመቱ ወጣት አትሌት በሪሁ የዚህን ርቀት ሁለተኛ ሰዓት ከማስመዝገቡ በተጨማሪ የኢትዮጵያን ፈጣን ሰዓት በ23 ሰከንድ በማሻሻል አዲስ ታሪክ መሥራት ችሏል። እሱን በመከተል ለአየርላንድ የሚሮጠው ኤፍሬም ግደይ በ28፡17 ሰዓት ሲገባ፣ ቶማስ ሞርቲመር ሦስተኛ ሆኖ አጠናቋል።




አትሌት በሪሁ አረጋዊ የ10 ኪሎ ሜትር የዓለም ሁለተኛ ፈጣን ሰዓት አስመዝግቧል፤

አትሌት በሪሁ "ውድድሩ ትልቅ በመሆኑ ስሜቴ የተደበላለቀ ነበር፤ ነገርግን የዓለም ክብረወሰንን ለመስበር ግብ አስቀምጬ ነበርም" ሲል ከውድድሩ በኋላ አስተያየቱን ሰጥቷል። "ውድድሩ በሙሉ ማለት ይቻላል ብቻዬን መሮጥ ቀላል አልነበረም፣ ነገር ግን ለኔ አስቸጋሪ የነበረው ነገር መንገዱ ጭቃማ መሆኑና ጠባቦቹ የመንገዱ መታጠፊያና ማቋረጫዎች ላይ እንዳልወድቅ ፈርቼ ነበር፣ ለማንኛውም በእውነት በጣም ረክቻለሁ" ሲልም ባለ ድሉ ተናግሯል። አትሌት በሪሁ በቶኪዮ ኦሊምፒክ በ10ሺ ሜትር አራተኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቁ ይታወሳል። እአአ ታኅሣሥ 2021 በባርሴሎና በተካሄደው የ5ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድርም የምንጊዜውም ፈጣን ሰዓት ባለቤት የሆነበትን ድል ማስመዝገቡ ይታወቃል።

ሌላኛው ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ድል ያደረጉበት ውድድር በፖርቹጋል ሊዝበን የተደረገ የግማሽ ማራቶን ውድድር ሲሆን ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በወንዶች አንደኛና ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቀዋል። በሴቶች ደግሞ አንደኛና ሦስተኛ ደረጃን ይዘው ጨርሰዋል።

በወንዶች መካከል በተካሄደው ውድድር አትሌት ንብረት መላክ 59፡06 በሆነ ሰዓት 1ኛ ደረጃን ይዞ ሲያጠናቅቅ አትሌት ሐጎስ ገብረሕይወት በተመሳሳይ 59፡07 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ በመሆን አጠናቋል። ሐጎስን በመከተል ቪኒሰንት ነግቲች ከኬንያ በ59፡10 ሦስተኛ ሆኖ ውድድሩን ጨርሷል።

በተመሳሳይ በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር አትሌት አልማዝ አያና 1፡05፡30 በሆነ ሰዓት አሸንፋለች። የሪዮ 2016 ኦሊምፒክ የ10 ሺ ሜትር ባለ ድሏ አልማዝ ለረጅም ጊዜ በጉዳት ከውድድር ርቃ ከቆየች በኋላ ከመም ውድድሮች ሙሉ በሙሉ ወጥታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የጎዳና ላይ ውድድሮች ትኩረት አድርጋለች። ከወራት በፊትም አምስተርዳም ላይ የመጀመሪያ የማራቶን ድሏን ያጣጣመች ሲሆን ተደጋጋሚ የግማሽ ማራቶን ውድድሮችን አድርጋ ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ችላለች። ባለፈው እሁድ ፖርቹጋል ላይ ስታሸንፍ ያስመዘገበችው ሰዓትም በግማሽ ማራቶን ታሪክ ሃያ አምስተኛው የዓለም ፈጣን ሰዓት ሆኖ ተመዝግቦላታል። አልማዝን በመከተል ማርጋሬት ቸሊሞ ከኬንያ ሁለተኛ ስትሆን ግርማዊት ገብረእግዚያብሔር በ1፡06፡28 ሦስተኛ በመሆን ውድድሯን አጠናቃለች።


### ማስታወቂያ

ያረጋል ደሬሳ ማርብል አምራች ድርጅት በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግስት መተከል ዞን ድባጤ ረዳ ፓርዘይት ቀበሌ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የእምነበረድ ማዕድን ምርመራ ለማካሄድ 29/06/2015 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መ/ቤታችንን ጠይቀዋል፡፡

**በመሆነም ለሚመለከው ጂኦግራፊክ ኮርድኔት ክልል፤**

**Block 1**

1. 36° 14' 57.41'E 10º 37' 10.24'N
2. 36º 14' 43.98'E 10º 37' 15.33'N
3. 36º 14' 50.41'E 10º 37' 20.46'N
4. 36º 15' 4.62'E 10º 37' 17.49'N

**Block 2**

1. 36º 15' 23.0'E 10° 37' 10.8'N
2. 36º 15' 23.4'E 10° 37' 12.0'N
3. 36º 15' 25.2'E 10° 37' 10.0'N
4. 36º 15' 24.0'E 10° 37' 05.5'N

ውስጥ በሚገኘው ቦታዎች ላይ ይገባኛል የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ በወጣ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለኢጀንሲያችን እንዲያቀርቡ እናሳስባለን፡

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ**

### ማስታወቂያ

ሆስፒስ ኢትዮጵያ መንግስታዊ ያልሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሲሆን ከዚህ በታች በተገለጸው የሰራ መደብ አመልካቾችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡

**የስራ መደቡ መጠሪያ** ክሊኒካል ነርስ
ብዛት፡- - አንድ
መስፈርት፡ - ከታወቀ ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ በነርሲንግ ሙያ በዲግሪ የተመረቀች/ የተመረቀ
- የሙያ ማረጋጫ (COC) እና የታደሰ የሙያ ፈቃድ ያላት/የለው
የሰራ ልምድ፡- - በሙያው ቢያንስ አንድ ዓመት በሙያው የሰራች/ የሰራ
ደመወዝ፡- - በስምምነት
የስራ ቦታ፡- - አዲስ አበባ
አመልካቾች

- ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ አስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን እያሳወቅን ከቀነ ገደብ በኋላ የሚመጡ እና የሚላኩ ማመልከቻዎችን የማንቀበል ከሆኑን ከወዲሁ እናሳውቃለን፡፡
- የትምህርት ማስረጃ እና ማመለከቻውን (CV) በመያዝ ወይም ከታች ባለው ኢሜል አድራሻ በመላክ ማመለከት ይችላል፡፡

አድራሻ፡- ወሰን ካራ በሚወስደው መንገድ አቤም ሆቴል አካባቢ ቤሰት ፔንሲዮን ጀርባ
ስልክ 0911-034186
ኢሜይል abathunephrem@yahoo.com and mesigul2016@gmail.com

**ሆስፒስ ኢትዮጵያ**

### የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
### የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥብ ግንባታ (GCB)

በአብክመ የከሚሴ ከተማ አስተዳደር ከተማ እና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት በ2015 በጀት ዓመት በአለም ባንክ በጀት የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥብ ግንባታ (GCB) ስራ በማሰራት በዘርፉ የንግድ ፈቃድ ያላቸውን ድርጅቶች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

**ስለሆነም በሥራው በመሳተፍ፡-**

13. ደረጃቸው GC/9 እና ከዚያ በላይ የሆኑት፣
14. ለስራው ህጋዊ አግባብነት ያለው ፈቃድ ኖሯቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉና የሳደሱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያላቸው/የቫት ተመዝጋበ የሆኑና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር TIN ያላቸው፡፡
15. የጨረታው ሰነድ ከከሚሴ ከተማ አስተዳደር ከተማ እና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 33 በግዢ/ፋይ/ንብ/አስ/ዋና የስራ ሂደት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እለት ጀምሮ 15/አስራ አምስት/ተከታታይ ቀናት ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ዋናና ኮፒ በመያዝ ዘወትር በስራ ቀንና ሰዓት በነፃ የጨረታ ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
16. ተጫራቾች የጨረታውን የፋይናንሽያል ሰነድዋና እና ኮፒ በማድረግ ለየብቻው በታሸገ ኤንቨሎፕ በአብክመ በከሚሴ ከተማ አስተዳደር ከተማ እና መሠረተ ልማት ጽ/ቤት በግዢ/ፋይ/ንብ/አስ/ዋና የስራ ሂደት በዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአስራ ስድስተኛው ቀን /16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 4፡00 ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ የጨረታ ሰነድ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
17. ጨረታው በቀን 21/7/2015ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት በግዢ/ፋይ/ንብ/አስ/ዋና የስራ ሂደት ቢሮ ተጫራቾች ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ በተገለጸው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ቀጠይ ባለው የስራ ቀን ይከፈታል፡፡
18. ተጫራቾች ተመላሽ የሚደረግ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 15454 /አስራ አምስት ሺህ አራት መቶ ሃምሣ ብር በጥሬ ገንዘብ ወይንም በተረጋገጠ በባንክ ትእዛዝ CPO ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና ማስያዝ አለባቸው፡፡
19. የጨረታ አሸናፊ የሆነው ድርጅት ውል በሚዋዋሉበት ጊዜ የውለታ ማስከበሪያ ከአጠቃላይ ድምር ዋጋ 10 % ማስያዝ ይኖርበታል፡፡
20. መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይንም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
21. ቢያንስ 3 እና በላይ በሆኑ በጨረታ አከፋፈት ወቅት ከተነበበው አጠቃላይ ዋጋ ላይ የሂሳብ ስሌት /አርቲሜቲክ ቼክ ከተሠራ በኋላ የተደረሰበት ልዩነት እስከ 2.5% ድረስ ከሆነ ተቀባይነት የሚኖረው ሲሆን ከዚህ የበለጠ ልዩነቱትካጋጠመ ከውድድር ውጭ ይሆናል፡፡
22. ከ3 በታች ከሆኑ በጨታ አከፋፈት ወቅት ከተነበበው አጠቃላይ ዋጋ ላይ የሂሳብ ስሌት/አርቲሜቲክ ቼክ/ ከተሰሩ በኋላ ከተደረሰበት ልዩነት እስከ 1% ድረስ ብቻ ተቀባይነት የሚኖረው ሲሆን ከዚህ በላይ ከሆነ ከውድድር ውጭ ይሆናል፡፡
23. የሂሳብ ስሌት /አርቲሜቲክ ቼክ/ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ባለሙያ ከሚስተካከለው ውጭ በተጫራቾች የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ ላይ በነጠላ ዋና ጠቅላላ ዋጋ ላይ ስርዝ ድልዝ ካለ ተጫራቹ ከጨረታ ውጭ ይሆናል፡፡
24. ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በከሚሴ ከተማ አስተዳደር ከተማ እና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት የግንባር በመቅረብ ወይንም በስልክ ቁጥር 0335540255 ደውሎ መረዳት ይችላሉ፡፡

**በአብክመ የከሚሴ ከተማ አስተዳደር ከተማ እና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት**